# የሙስና ወንጀል መርማሪዎችና አቃቢያነ ህግ የሙያ ስነምግባር

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሰኔ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ፡
ኢትዮጵያ

## ምህጻረ ቃላት

**የወ/መስ/ስ/ሕ--- የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ህግ**

**የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/አ---- የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአት አዋጅ**



## ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

1. ስለስነምግባርና የሙ-ያ ስነምግባር በጠቅላላው ...... 7
1.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ ...... 7
1.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማ ...... 7
1.2.1. የምዕራፉ ዝርዝር ዓላማዎች ...... 7
1.3. የስነምግባር ትርጉም ...... 8
1.4. እሴትና መርሆች ...... 11
1.5. ሙያና የሙ-ያ ስነምግባር ...... 13
1.6. የፍትህ አካላት ተገልጋዮች የአገልግሎት እርካታ መገለጫዎች ...... 16
ክፍል ሁለት ...... 20
የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች የስነምግባር መርሆዎች ...... 20
2.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ ...... 20
2.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች ...... 20
2.2.1. የምእራፉ ዝርዝር አላማዎች ...... 20
2.3. የስልጠናው ይዘት ...... 21
2.4. አቃቤ ህግ የሚፈጽመው ቃለመሀላ ...... 21
2.5. የፖሊስ ተቋም አላማና ግብ ...... 22
2.6. የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች የስነምግባር መርሆዎች ...... 22
2.6.1. ሙያዊ ነፃነት ...... 22
2.6.2. በአድሎአዊነት አለመስራት ...... 29
~~2.6.3.~~ የሙ-ያ ብቃትና ትጋት ...... 34
2.6.4. ሀላፊነትና ተጠያቂነት ...... 39
2.6.5. ቅንነት ...... 40
2.6.6. ሀቀኝነት ...... 44
2.7. ሙያዊ ስነምግባርን ለማዳበርና ለማጠናከር ባህርያዊ እና ተቋማዊ ድጋፎች ...... 48
ማጣቀሻ ጽሁፎች/ዋቢዎች ...... 54

# አጠቃላይ መግለጫ

## መግቢያ

የሙስና ወንጀልን በመመርመርና በመክሰስ ስራ የተሰማሩ መርማሪዎችና አቃቤ ህጎች በህግ የተጣለባቸውን ሀላፊነት በብቃት ለመወጣት ሙያው የሚጠይቀውን የሙያ ስነምግባር አውቀውና የራሳቸው አድርገው ሲተገብሩት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣ የሙያ ስነምግባሩ ካልተከበረ ደግሞ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው፡፡ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች (መርማሪዎችና አቃብያነ ህጎች) ስራ የሙያ ስራ ስለሆነ እንደማንኛውም ሙያ ባለሙያዎች ስራቸውን ሲሰሩ የሚፈለገውን የመጨረሻ ውጤት (የህግ የበላይነትን በማስከበር ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የማረጋገጥ) ለማምጣት ሊያከብሯቸው የሚገቡ የሙያ ስነምግባር ግዴታዎች አሉ፡፡ ለዚህ የስልጠና ሞጁል ዝግጅት ግብአት ለማሰባሰብ በተደረገ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ወቅት በተደጋጋሚ ከተነሡ ነጥቦች ወይም ጉዳዮች መካከል መርማሪዎችም ሆኑ አቃቤ ህጎች ሙያው የሚጠይቀውን ስነምግባር በተመለከተ የእውቀትም ሆነ የክህሎት ክፍተቶች እንደሚታዩባቸው ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ስልጠና ሊሰጣቸው እንደሚገባ የዳሰሳ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ይህ ሞጁልም የተዘጋጀው በዚህ የዳሰሳ ጥናት የተሰባሰበውን ግብአት መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ሞጁሉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በክፍል አንድ በአጠቃላይ ስለስነምግባር ምንነት፣ እሴትና መርሆ፣ የሙያ ትርጉም እና የሙያ ስነምግባር ምንነት፣ እንዲሁም የፍትህ አካላት ተገልጋዮች/ተጠቃሚዎች ማንነት እና ከፍትህ አካላት የሚፈልጉት የአገልግሎት አይነት ምን እንደሆነ በቀጣይነት ለፖሊስና ለአቃቤ ህግ የሚመሩባቸው የስነምግባር መርሆዎች በአጭሩ የቀረበበት ነው፡፡ በክፍል ሁለት የፖሊስ/መርማሪዎች እና የአቃቤ ህግ የሙያ ስነምግባር የሚዳስስ ነው ፡፡

ሞጁሉ ስለሙያዊ ነጻነት፣ ከአድልዎ በጸዳ መልኩ ስለመስራት፣ የሙያ ብቃትና ትጋት፣ ሀላፊነትና ተጠያቂነት፣ ቅንነት፣ ሀቀኝነት መርሆዎች እንዲሁም እነዚህ የስነምግባር መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ ሊደግፉ የሚያስፈልጉ መዋቅራዊ ድጋፎችን ባካተተ መልኩ ቀርቧል፡፡

# የሥልጠናው ይዘቶችና አወቃቀር  እና የስልጠና ስነ-ዘዴ

ሥልጠናው የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ በሁለት ምእራፎች የተከፈሉ ይዘቶች ተካተውበታል። የመጀመሪያው ምእራፍ ስለስነምግባርና የሙያ ስነምግባር በጠቅላላው የተመለከተ ነው። ሁለተኛው ምእራፍ የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች  የስነምግባር መርሆዎች የተመለከተ ነው።

ሠልጣኞች በሥልጠናው ሂደት፣ የጎላውን ድርሻ ወስደው፣ ጥያቄዎችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት፣ በጥያቄዎች ዙሪያ በመወያየት፣ ተጨማሪ የሐሳብ ግብዓቶችን በማምጣት፣ ተመክሮዎችን በማካፈል ሃሳቦችንም በማፍለቅ የእርስ በእርስ ተሞክሮዎቻቸውን በመለዋወጥ በንቃት የመሳተፍ እድል በመፍጠር መልኩ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡በዚህም ሰልጣኞች  በዕለት ከዕለት የስራና የሙያ ኃላፊነትን ሲያከናውኑ  ሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል የላቀ ሚና እንዲወጡ ይጠበቃል።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሥሩ ንዑሳን ርእሶችን ያቅፋል። አንድ ርእስ በማነቃቂያ ጥያቄዎች ይጀምራል። ጥያቄዎቹ የሠልጣኞችን ተሳትፎ የሚያበረታቱ ናቸው። ከማነቃቂያ ጥያቄዎቹ ቀጥሎ አጫጭር ማብራሪያዎች ይቀርባሉ። በየምዕራፉ መጨረሻ አስረጅ ናሙናዎች እና  የማጠቃለያ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህ ጥያቄዎች፣ ሠልጣኞች የተወያዩባቸውን ሐሳቦች በርግጥ በተገቢው ደረጃ መረዳታቸውን የሚፈትሹ ናቸው።

ስልጠናው በአቀራረቡም **አሳታፊ የሥልጠና ሥነዘዴን** የተከተለ ነው ሲሆን በዚህም ስነዘዴ፡-

- እያንዳንዱ ንዑስ ርዕሶችን የማነቃቂያ ጥያቄዎች ላይ ሰልጣኞችን በግልና በአነስተኛ ቡድን ወይም በጎንዮሽ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በንቃት ማሳተፍ
- በጉዳዮች ላይ ማብራሪያዎችን መስጠት፣
- በአስረጅ ናሙናዎች እና በምዕራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ውይይት ማቅረብ፣
- ሰልጣኞችን የነቃና ሳቢ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን  ሁኔታን ማመቻቸት፣

ስለሆነም በመወያያ ጥያቄነት  እየተሰጡ በቡድን ጥልቅ ውይይቶች በማድረግ   መሠራት የሚኖርባቸው መሆናቸውን ከወዲሁ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

## የሥልጠናው አጠቃላይ መገምገሚያ ስልት

በዚህ የስልጠና ሞጁል እያንዳንዱን አላማ ሰልጣኞች በሚገባ ስለመገንዘባቸው እና ስለመረዳታቸው እና በስልጠናው የተቀመጠውን ለውጥ ስለማሳካታቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ዘዴዎችን የምንጠቀም ሲሆን ፡-

1. ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገምግም የቅድመ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስቶች በሰነዱ ላይ አባሪ የተደረገውን በመምረጥ ግምገማ የሚካሄድ ይሆናል፡፡
2. በስልጠናው ጊዜ ሰልጣኞች በማነቃቂያ ጥያቄዎችን እና በምዕራፉን የማጠቃለያ ጥያቄዎች የሚገመገሙ ይሆናል
3. ከስልጠና በኋላ ሰልጣኞች የሚጠበቅባቸውን እውቀት እና ክህሎት ስለመጨበጣቸው የሚረዳ የመመዘኛ ጥያቄ ስልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ በኮሚሽኑ የስልጠና ጥራትና ተገቢነት ዴስክ ስር በሰነዱ ዙሪያ በሚያዘጋጇቸው የጽሁፍ ፈተናዎች እና በድህረ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስቶች መሰረት ሰልጣኞች የሚመዘኑ እና የሚገመገሙ ይሆናል፡፡

## አጠቃላይ አላማ

የሙስና ወንጀልን በመመርመርና በመክሰስ ስራ ላይ የተሰማሩ መርማሪዎችና አቃቤ ህጎች የሙያ ሥነ-ምግባር እሴቶችን እና መርሆችን በግል ህይወታቸውና በሥራ ቦታቸው ተግባራዊ በማድረግ በህግ የተጣለባቸውን ሀላፊነት በብቃት በመወጣት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ይከላከላሉ፡፡

## የስልጠናው ተተኳሪዎች

በዚህ ሞጁል የሙስና ወንጀል በመመርመር እና በመክሰስ ስራ ላይ የተሰማሩ ፖሊሶች እና አቃቤ ህጎች የሚሰለጥኑበት ሰነድ ነው፡፡

## በሞጁሉ የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች

በዚህ የስልጠና ሞጁል የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ ዙሪያ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ያላቸው እና በዘርፉ የሰሩ (ማለትም በመርማሪነት

፣በአቃቤ ህግነት) እና በኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ያሰለጠኑ ሆነው ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የስልጠና ሞጁሉን ለመሸፈን የተዘጋጀ ግምታዊ የሰአት ድልድል

ይህንን የስልጠና ሞጅል ለማሰለጠን ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው የስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የሚካተት ሲሆን ለእያንዳንዱ የሞጁሉ ምዕራፍ የተሰጡት ሰአቶች ግምታዊ ሰአቶች ናቸው፡፡ ስልጠናው ይሰጣል ተብሎ የተገመተው **አንድ ቀን** ሲሆን በአማካይ በአንድ ቀን የስልጠና ውሎ ውስጥ **6 ሰዓት** ያህል ለስልጠና ይውላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም ለዚህ የስልጠና ሞጅል አጠቃላይ የተሠጠው ግምታዊ ጊዜ 6፡00 ሰአት ሲሆን ለእያንዳንዱ ምዕራፍ የተሠጠው ሠዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ❖ ምእራፍ አንድ ስለስነምግባርና የሙያ ስነምግባር በጠቅላላው (የተሠጠው ግምታዊ ሰዓት 2፡00)
- ❖ ምእራፍ ሁለት የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች የስነምግባር መርሆዎች (የተሠጠው ግምታዊ ሰዓት 4፡00)

# ምእራፍ አንድ

## 1. ስለስነምግባርና የሙያ ስነምግባር በጠቅላላው

### 1.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ

በዚህ ሞጁል ስለስነምግባር ትርጉም፣ እሴትና መርሆ ምንነትና ከስነምግባር ጋር ስላለው ግንኙነት፣ የሙያ ስነምግባር ምንነትና መገለጫዎቹ፣ የፍትህ አካላት ተገልጋዮች እና የተገልጋዮች መሰረታዊ የፍትህ ፍላጎቶች ምንነት በአጭሩ ይቀርባል፡፡

### 1.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማ

የሥልጠናው ተሳታፊዎች የዚህን ምእራፍ ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ❖ ሰልጣኞች የሙያ ሥነ-ምግባር እሴቶችን እና መርሆችን በግል ህይወታቸውና በሥራ ቦታቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

#### 1.2.1. የምዕራፉ ዝርዝር ዓላማዎች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡እነርሱም፡-

- ስለስነምግባር ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የሙያ ስነምግባር ይተገብራሉ፡፡
- የሙያ ስነምግባር አስፈላጊነት በመስራት ያሳያሉ፡፡
- የተገልጋዮች የአገልግሎት እርካታን ይመዝናሉ

**የምዕራፉ ይዘት**

ሥልጠናው የሚከተሉትን ይዘቶችን ያካትታል፡፡

- የስነምግባር ትርጉም
- እሴትና መርሆች
- ሙያና የሙያ ስነምግባር
- የፍትህ አካላት ተገልጋዮች የአገልግሎት ርካታ መገለጫዎች

## 1.3. የስነምግባር ትርጉም

Ethics የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን የመጣውም ethos ከሚል የግሪክ ቃል ነው፡፡ በግሪክ ቋንቋ ethos ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ቦታ የሚል ትርጓሜ የነበረው ሲሆን፣ ቀስ በቀስና በጊዜ ሂደት አጠቃቀሙ ልምድ፣ ጸባይ፣ ባህርይ፣ የአስተሳሰብና የአነጋገር ዘይቤ የሚሉ ትርጉሞችን እንደያዘ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡[1]

በጥንታዊቷ ሮም በላቲን ቋንቋ የግሪኩ ቃል የethos አቻ ቃል mos የተባለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም ከሞላ ጎደል ከ ethos ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በተጨማሪ ህግ ደንብ ያለባበስ ስርአት ወዘተ የሚሉ ትርጉሞችን ይይዛል፡፡[2]

Morality የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘውም ከዚሁ *moralitas*, ከተባለው የላቲን ቃል ነው፡፡ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሞራል እና ኤቲክስ ተመሳሳይ ሀሳብን ለመግለጽ በመቀያየር ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ይህ ኤቲክስ የተባለው ቃል በአማርኛ ስነምግባር ተብሎ ይታወቃል፡፡

**የስነምግባር ትርጉም፣**

የብላክስ ሎው ዲክሽነሪ ስነምግባር እንደሚከተለው ይተረጉማል፡፡ "አንዱ ለሌላው ያለውን የሞራል ግዴታ የሚመለከት)

በኦክስፎርድ ዲክሽነሪ የሚከተለውን ትርጉም እናገኛለን፡፡ የአንድ ሰውን ባህርይ ወይም ጸባይ የሚመሩ የሞራል መርሆዎች)፡፡ስለትክክልና ትክክል ስላልሆነ እምነት መርህዎች የሚደነግጉ የሞራል መርሆዎች)

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት ውስጥ** መልካም ጸባይ (አድራጎት)፣ በአንድ የሙያ መስክ ካለ ባለሙያ የሚጠበቅ አድራጎት ወይም አሰራር፣አንድ ሀሳብ ወይም ድርጊት መልካም ወይም መጥፎ፣ ትክክል ወይም ስህተት፣ዋጋ ያለው ወይም የሌለው፣ ፍትሐዊ ወይም ኢ-ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጫ ነው በሚል ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

---

[1]Wikipedia, The English word *ethics* is derived from the Ancient Greek word *ēthikós* (ἠθικός), meaning "relating to one's character", which itself comes from the root word *êthos* (ἦθος) meaning "character, moral nature"

[2] Wikipedia- **Morality** (from Latin: *moralitas*, lit. 'manner, character, proper behavior') is the differentiation of intentions, decisions and actions between those that are distinguished as proper (right) and those that are improper (wrong).

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ትርጉሞች በአጭሩ የሚያመለክቱት ስነምግባር በሁለት አይነት መልኩ ጥቅም ላይ እንደሚውል ነው፡፡

አንደኛው ለሰው ልጅ ትክክል እና ትክክል ያልሆነው ምግባር (ሀሳብ፣ ድርጊት) ምንድነው? ይሄኛው ምግባር ትክክል ነው ያኛው ደግሞ ትክክል አይደለም የምንለው ከምን ተነስተን ነው? ምክንያታችን ምንድነው? የሚለውን የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡

ሁለተኛው ትርጉም በጎ እና ክፉ፣ ወይም ትክክለኛ እና ትክክለኛ ያልሆነ ባህርይን ወይም ጠባይን የሚያመለክት ወይም እነዚህን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የምንመራበት ደንብ፣ ህግ ወይም መመሪያ ነው፡፡

ሰው በተፈጥሮው እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን እየመረጠ (ይሄንን ላድርግ ይሄንን አላደርግም) እና የመረጠውን ውሳኔ ተግባራዊ እያደረገ የሚኖር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ሊኖር አይችልም፡፡ ሳይመርጥ፣ ሳይወስን መንቀሳቀስ ካልቻለ፣ ጥያቄው የሚሆነው በምን መመሪያ፣ በምን የስነምግባር ደንብ መሰረት ምርጫውን ይወስናል? የሚለው ነው፡፡

የሰው ልጅ ከልጅነቱ ጀምሮ ያዳበረው ባህርይ አለው፡፡ ይህ ባህርይ የተገነባው ከልጅነቱ ጀምሮ ከቤተሰቡ፣ ከአብሮ አደግ ጓደኞቹ፣ ከመንደሩ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከስራ ቦታ ወዘተ… ከሚያገኘው መረጃ በመነሳት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተገነባው ጠባዩ አውቆም ሆነ ሳያውቅ በውስጡ ከራሱ ውስጣዊ ህሊና ጋርም ይሁን ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ ሀሳቦችና ድርጊቶችን የሚለይ መመዘኛ ያለው ነው፡፡

እነዚህ አብረውት ያደጉት መመዘኛዎች የተገነቡት ከልጅነቱ ጀምሮ በሚመርጣቸውና በሚወስዳቸው እርምጃዎች በሚያገኛቸው ሽልማቶችና ቅጣቶች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ እነዚህ ሽልማቶችና ቅጣቶች ውስጣዊ እና ውጫዊ ናቸው፡፡ ውስጣዊ የሚባሉት በህሊናው እርካታ ማግኘቱ ወይም አለማግኘቱ ራስን መውቀስና መጸጸቱ) ሲሆን ውጫዊ የሚባሉት በቤተሰቡ በአካባቢው ሰዎች በአስተማሪዎች በጓደኞች ወዘተ የሚያገኛቸው እውቅና (ጎሽ የሚል እውቅና፣ ቁንጥጫ፣ ግልምጫ፣ ኩርፊያም ወዘተ) ናቸው፡፡

ሰው በዚህ መልኩ አብሮት ያደገው ጠባዩ እና ጠባዩ የሚመራባቸው መርሆዎች ለራሱ ለሰውየው ትክክለኛ ጠቃሚ ወይም ጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መርሆዎች ተሰርተው የሚያልቁበት ጊዜ የለም፡፡ እስከእለተ ሞት ድረስ የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ ይሁንና መቀጠሉ ከጊዜ

ወደጊዜ መሻሻል ያመጣል ማለት አይደለም፡፡ ወይ ወደመሻሻል ወይም ወደባሰ ሁኔታ እየገባ ሊሆን ይችላል፡፡

ምርጫው በስነምግባር መርሆዎች የመመራትና ያለመመራት ጉዳይ ሳይሆን፣ ትክክለኛው የስነምግባር መመሪያ የትኛው ነው? አሁን የያዝኩትን ልቀጥልበት ወይስ ላሻሽለው ልቀይረው? የሚለው ላይ ነው፡፡

መልካምና ክፉ ተግባርን ወይም ሊደረግ የሚገባና የማይገባን ሀሳብ፣ ተግባር ወይም ንግግርን የሚመለከቱ ስርአቶች ወይም ደንቦች ሁሉ በስነምግባር ትርጉም ውስጥ የሚጠቃለሉ አይደሉም፡፡

በርካታዎቹ የመልካምና ክፉ ባህርያት መርሆዎች፣ ስርአቶችና ደንቦች በአንድ ጊዜ ስነምግባራዊ፣ እና ህጋዊ የሚሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ ብዙውን ጊዜ ሌላውን ሰው መግደል መጥፎነቱ በህግ ብቻ ሳይሆን፣ በብዙ ሰዎች የህሊና እምነትም ትክክል ያልሆነና ሐጢያት እንደሆነ ተደርጎ ይታያል፡፡ ስለሆነም የህጋዊ ስርአቱም፣ የስነምግባራዊ ስርአቱም ክፍል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ስነምግባርና ህግ ተመሳሳይ አይደሉም፡፡ ልዩነታቸውን ስናይ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| ስነ ምግባር | ህግ |
|---|---|
| ስልጣኑ ዉስጣዊ ነዉ፣ | ስልጣኑ ዉጫዊ ነዉ፣ |
| ፍርድ የሚሰጠዉ የስነ ምግባር መርሆዎችን ወይንም ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ ነዉ | ፍርድ የሚሰጠዉ ህጋዊ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ነዉ ፣ |
| አብዛኛዉ ስነ ምግባራዊ የሆነ ጉዳይ በህግ ያልተሸፈነ ነዉ | አንዳንድ ጊዜ ህግ ኢ- ስነ ምግባራዊ ሊሆን ይችላል፣ |

## 1.4. እሴትና መርሆች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የእሴቶች መኖር እና መከበር ለመርማሪዎች እና አቃቤ ለህግ ባለሙያዎች የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?

የሰው ልጅ የመንፈስ ፍላጎቱ ሕይወቱ ደስተኛ እና የረካ፣ ከጭንቀት፣ ከራስ መውቀስ ነጻ መሆን ነው፡

ከስነምግባር አንጻር በግልጽም ይሁን በዝምታ የሰው ልጅ ሳይመልስ የማያልፋቸው ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡

የመጀመሪያው ጥያቄ የማደርገውን ነገር የማደርገው ወይም እንዲህ ማድረግ ይገባኛል የምለው በመጨረሻ ምን ለማግኘት ነው? ወይም የመጨረሻ የህይወት እሴቱ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ እነዚህ የመጨረሻ እሴት የሚገልጹ ምሳሌዎች፣

- ከሞት በኋላ ዘላለማዊ ህይወት፣
- እስከ ህይወት ፍጻሜ የማንም ጥገኛ ሳይሆኑ ነጻነትን ጠብቆ መቆየት፣
- ጥሩ የህግ ባለሙያ መሆን፣
- ሰዎች ከችግር ወጥተው ማየት ወዘተ ናቸው፡፡

የሰው ልጅ ለዚህ ለምንድነው የምኖረው? በመጨረሻ ምን ለማግኘት ነው? የሚለውን ጥያቄ ላለመመለስ ለመሸሽ ቢሞክርም ሳይመልሰው ሊኖር አይችልም፡፡ በዝምታ መልሱ መቀመጡ አይቀርም፡፡ ከሚያደርገው ድርጊት የመጨረሻ ግቡ ይመዘዛል ወይም ይደረጋል፡፡

ሁለተኛው ጥያቄ ይህንን የመጨረሻ እሴቱን እውን ለማድረግ ምን ማድረግ አለብኝ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ሁለት ጥያቄዎች አሉ፡፡ ለማን? ምን? ሳደርግ ነው የመጨረሻ የህይወት እሴቴ ላይ የምደርሰው ወይም የማደርገው? የሚለው ነው፡፡

ለማን? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ከዚህ አንጻር በአለም ላይ በስነምግባር ዙሪያ የተመራመሩ ወይም የጻፉት በሚከተሉት ሶስት ትላልቅ ጎራዎች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ አንደኛው ሄዶኒዝም የሚባለው የስነምግባር ጥናት ዘርፍ የስነምግባር የመጨረሻ ግብ ለፈጻሚው ደስታንና ምቾትን ማስገኘት አለበት የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ዩቲሊታሪያኒዝም አንድ ስራ ጥሩ ሊባል የሚችለው ጥቅም ሲኖረው ብቻ ሳይሆን በሚቻል አኳኋን አብዛኛውን ሰዎች የሚጠቅም ሲሆን ነው፣

ያለበለዚያ አንዱን ሰው ብቻ ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ ከሆነ መልካም ስራ ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ዲኦንቶሎጂ ደግሞ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ሁልጊዜም የፈጣሪን ፈቃድ/ የተፈጥሮ ህግ የሚለንን ማድረግ አለብን፣ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ፈጣሪ ያዘዘውን ካደረግን ትክክል አደረግን ማለት ነው የሚል ነው፡፡[3] ነገር ግን ምርጫዎቹ በእነዚህ ብቻ ይወሰናሉ ማለት አይደለም፡፡ በዚህ ጽሁፍ ለቀረበው ሀሳብ መሰረታዊ ጽንሰሀሳቡን ለመረዳት ግን እነዚህ በቂ ናቸው፡፡ ለማንኛውም ስነምግባር ሊመልሳቸው ከሚገቡ ጥያቄዎች አንዱና መሰረታዊው ተጠቃሚው ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚመለሰው ሶስተኛው ጥያቄ ምን ሳደርግ? ነው የመጨረሻ የህይወቴን እሴት የማገኘው የሚለውን መመለስ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች ከሚሰጠው መልስ የሚመነጭና የሚመዘዝ ነው፡፡

ሁሉም መንገድ ወደምትፈልገው ግብ አያመራም፡፡ ትክክለኛ መንገድና አቅጣጫ፣ (ሀሳብ፣ ንግግር፣ ድርጊት) ሲሆን፣ ከዚህ ውጭ ያለው ሁሉ የተሳሳተ ይባላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት በምሳሌነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

- ዘላለማዊ ህይወትን ለማግኘት ቅዱስ መጽሀፍ የሚያዛቸውን ህግጋት አክብሮ መፈጸም፣
- የራስን ነጻነት ጠብቆ ለመኖር ስራን መውደድና መስራት፣
- ገንዘብን በአግባቡ መያዝና መቆጠብ፣
- ከመዋሸት መቆጠብና ሁልጊዜ እውነትን መናገር፣
- ያለውን ለሌላው ማካፈል ወዘተ

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች የምንሰጣቸው መልሶች ትክክል ወይም ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ትክክል ከሆነ ወደምንፈልገው እንደርሳለን፡፡ ካልሆነ ደግሞ አንደርስም፡፡ መልሱ ትክክል አለመሆኑ ማረጋገጫው በተግባር በመተግበር ምላሽ የምንሰጠው ራሳችን ነን፡፡ እንደምንፈልገው አለመሆኑ ሲሰማን እንግዲህ ጤነኛ ሰዎች ነንና እነዚህን ደጋግመን ደጋግመን እየከለስን እየመረመርንና እያረምን ወደምንፈልገው ለመድረስ እንሞክራለን፡፡

[3] Wikipedia, Ethics

በአጭሩ የትክክለኛ ስነምግባር ማረጋገጫና መለኪያ መስፈርት ስነምግባር በማክበሬ በመጨረሻ ምን ለማግኘት ነው? ለማን? ምን ሳደርግ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስና ምላሹን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

እያንዳንዱ ድርጊት (የምንናገረው ንግግር፣ የምናደርገው ድርጊት) ውጤት አለው፡፡ ውጤቱ እንዲሆን የተመኘነውና የምንፈልገው ወይም ከምኞታችን ውጭ ያልጠበቅነው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ውጤት ተጠቃሚ የሚያደርገው ወይም ተጎጂ የሚያደርገው ወገን መኖሩ አይቀርም፡፡ የዚህ ውጤት ደግሞ አለ (ራስን የመቻል ወይም የሰዎች ጥገኛ መሆን፣ ወደዘላለማዊ ህይወት መሄድ ወይም አለመሄድ)፡፡

ከልጅነታችን ጀምሮ በልምድ የዳበረው (ባህርያችን) እኛን የሚመራን ለእነዚህ ጥያቄዎች በሰጠው መልስ መሰረት ነው፡፡ የየራሳችንን ባህርያችንን ብንመረምረው ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱ ምን እንደሆነ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ እነዚህን ጥያቄዎች በግልጽ ወይም በዝምታ እየመለሰ እና እየተገበረ ይኖራል እንጂ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ድርጊታችን የሚያመጣቸው ውጤቶች እርስ በራሳቸው የሚጋጩ አንዱ ሌላው ጋር የሚቃረኑ ከሆነ ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው በውስጣችን ለእነዚህ ጥያቄዎች እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ መርሆዎችን የምንተገብር ሆነን ጠባያችን በመቀረጹ በመገንባቱ ነው፡፡

### 1.5. ሙያና የሙያ ስነምግባር

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. በመርማሪዎች እና በአቃቤያነህጎች የሙያ ስነምግባር መላበስ ተገልጋዩ ማን ነው?
2. የተገልጋዮች የፍትህ አገልግሎት ርካታ መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

ሙያ በትምህርት፣ በስልጠና ወይም ስራውን በመስራት በልምድ የሚገኝን ንድፈ-ሀሳባዊ እውቀት፣ክህሎትን የሚመለከት እና በሙያው ውጤት ተጠቃሚ ለሚሆነው ወገን ወይም አገልግሎት ጠያቂ ተጨባጭ ጠቀሜታ የሚሰጥ ስራ ነው፡፡

በሙያ አገልግሎት ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጥ እና ሙያዊ አገልግሎት የሚቀበል ሁለት ወገኖች አሉ፡፡

*የሙያው ተጠቃሚዎች ከሙያው የሚፈልጉት አለ፡፡ (ታማሚዎች ከህመም መዳን፣መጠለያ የሚፈልጉ መኖሪያ ቤት መስራት፣በወንጀል የተጎዱ ጥፋተኛ ካሳ እንዲከፍል ወይም እንዲቀጣ ወዘተ… )*

*ባለሙያዎች አገልግሎቱን ሲሰጡ ለተጠቃሚው የሚፈልገውን ማድረግ ነው፡፡ ህክምና ታማሚን ማዳን ነው፡፡የህግ ማስከበር አገልግሎት ውጤት ወንጀል አድራጊዎች ወይም አጥፊዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ወይም ካሳ እንዲከፍሉ በማድረግ የሰዎች ሰብአዊ መብት እንዳይጣስ ወይም እንዲከበር ወይም ወደ ነበረበት ቦታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡*

*ባለሙያው ለተጠቃሚው አገልግሎቱን እሰጣለሁ ብሎ ሲስማማ እነዚህን ተጠቃሚው የሚጠይቀውን ውጤት ለማምጣት ነው፡፡ስለሆነም ተጠቃሚው ከሚፈልገው ውጤት የተለየ እንዳይመጣ አላስፈላጊ እንዳይኖር ወይም እንዲቀንስ ተስማምቷል ማለት ነው፡፡*

*ይህንን ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ባለሙያው ሊያደርጋቸውና ከማድረግ ሊቆጠባቸው የሚገባ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ሙያውን የሚተገብረው የሚያውቀው እንጂ ባለሙያ ያልሆነ የሚያውቀው ወይም እንዲያውቀው የሚጠበቅ አይደለም፡፡ የህክምና ሙያ ባለቤት ሰውን ለማዳን ሊያከብራቸው የሚገባ እና ሊያደርጋቸው የማይገባ ተግባራት አሉት፡፡ለምሳሌ መርፌ ሲወጋ እንዴት እንደሚወጋ የሚያውቀው ባለሙያው ብቻ ነው፡፡አንድ ባለሙያ ያልሆነ ሰው ለምን እዚህጋ ትወጋለህ? ብሎ ለመቃወም እውቀት የለውም፡፡ ባለሙያው የሙያ ስነምግባሩን ካላከበረ ሙያው የሚፈልገው ውጤት አይመጣም፡፡ በህክምና ሙያ ወይ ታማሚው አይድንም ወይም ይሞታል ወይም ሌላ አላስፈላጊ በሽታ ወይም ችግር ይከሰታል፡፡ ስለሆነም ቃሉን አላከበረም ማለት ነው፡፡*

*ይህ ባለሙያ በሙያው ሊያደርግ የሚገባውን ወይም ሊያደርግ የማይገባውን ተግባራት የሚገዙት መርሆዎች የሙያ ስነምግባር ይባላሉ፡፡ የሙያ ስነምግባር ማለት ሙያው በራሱ እንዲተገበር የሚያስገድደውን የሙያው አባላቶች እንደባለሙያ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያውቁትን የሙያው መርሆዎች ማለት ነው፡፡ የሙያ ስነምግባር ተገልጋዩ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ አድርግ የሚል አይደለም፡፡ ነገር ግን በሙያው የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚጠይቀውን ብቻ አድርግ የሚል ነው፡፡*

በአዋጅ ወይም በደንብ የዚህ ሙያ ስነምግባር ይሄ ነው ያ ነው ሊባል ይችላል፡፡ይሁንና የሙያ ስነምግባር ምንጩና መሰረቱ ራሱ ሙያው እንጂ አዋጅ ወይም ደንብ አይደለም፡፡ አዋጅ ወይም ደንብ ሙያው የሚጠይቀውን ስነምግባር በህግ ደረጃ ሊዘረዝረው ይችላል፡፡ በአዋጅ ወይም በደንብ ስላልተጻፈ ግን የሙያ ስነምግባር የሚባል የለም ወደሚል ድምዳሜ አይደረስም፡፡ በአዋጅ እውቅና ተሰጠውም አልተሰጠውም ሙያው የተቋቋመለትን ወይም ሊያመጣው የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያስፈልገውን የሙያ ስነምግባር መኖሩን አያስቀረውም፡፡

በሙያ ማገልገል ማለት ከሌሎች ሰዎች ጋር ቃልኪዳን መፈጸም (ውል መፈጸም) ማለት ነው፡፡ የግል የስነምግባር ደንቦቼን ለሌሎች በሙያ ለማገልገል በገባሁት ቃል ውስጥ አሳካለሁ ብሎ ቃል እንደመግባት ነው፡፡ የሰዎችን ሰብአዊ መብት አከብራለሁ፡፡ ከተስማሙት ውጭ አልፈጽምም ማለት ነው፡፡ የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ እንደማለት ነው፡፡ እኔ ሰው ነኝ፣ እመኑኝ አታላይ አጭበርባሪ አይደለሁም፣ ቃሌን የማጥፍ ሰው አይደለሁም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም አይጋጨም፡፡ ማንም ሰው በሌላ ሰው ህይወት ላይ የግል እምነቱን የመጫን መብት የሌለው በመሆኑ፣ የግል ስነምግባር መመሪያውም የሌሎች ሰዎችን መብት በሚጥስ መልኩ (የገባውን ቃል መልሶ በሚጥስ እና ሌሎችን በማታለል ላይ) የተገነባ ከሆነ ችግሩ ያለው የግል ጠባዩ (ስነምግባሩ) ላይ እንጂ ሙያውን በመተግበር ላይ አይደለም፡፡ ባለሙያ የገባውን ቃልን ባለማክበር የሚገኝ ጥቅም አለ? ቁሳዊ ጥቅም ሊያገኝ ይችላል፡፡ የሰው ኪስ ውስጥ ለመግባት መጀመሪያ ራስን በነፍስ ሌባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡[4]እራስን ማዋረድ ያስፈልጋል፡፡ የራሴን ህሊና ሳላቆሽሽ በሌላ ላይ ወንጀል መፈጸም አልችልም፡፡ ቃሉን የማያከብር ከወንጀለኛ በምን ይለያል?ወንጀለኛ ማለት እኮ አልፈጽምም ብሎ በአደባባይ ቃል የገባውን የሚጥስ ነው፡፡ የሕሊናን ንጽህና ገድሎ ቁሳዊ ጥቅም ማግኘት ይሻላል ወይስ የህሊናን ንጽህና ጠብቆ በዚህ ውስጥ ቁሳዊ ጥቅምን ለማግኘት መወሰን? ምርጫው እነዚህ ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ምርጫ የለም፡፡ ስለሆነም ክፍያ የሌለው ጥቅም የለም፡፡

[4]The works of Epictitus, p. 99

## 1.6. የፍትህ አካላት ተገልጋዮች የአገልግሎት እርካታ መገለጫዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የፍትህ አካላት ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጣቸው መርካታቸውን የሚያሳዩ የእርካታ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

የፍትህ አካላት ተገልጋይና ተጠቃሚው በአገሪቱ የሚኖረው ነዋሪና ጠቅላላው ህብረተሰብ ነው። ተጠቃሚው ህብረተሰብም እንደግለሰብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ እና እንዳይጣሱ፣ በጋራ ደግሞ የጠቅላላው ህዝብ ሰላምና ደህንነት እንዲጠበቅ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ይፈልጋሉ።

የህግ የበላይነትን ማስከበር ማለት በዋነኛነት ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ በመጠበቅ የጋራ ሰላምና ደህንነትን ማስጠበቅ ነው። በስራ ላይ ያለውን የወንጀል ህግ በዝርዝር ስንመለከተው የምናገኘው ሀቅም በጣም የሚበዙት ያስቀጣሉ ተብለው የተደነገጉት የወንጀል ድርጊቶች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶች መሆናቸውን ነው። በወንጀል ሕጉ (የደንብ መተላለፍን ሳይጨምር) ካሉት ጠቅላላ 496 የወንጀል ድንጋጌዎች 346 ወይም ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሰብአዊ መብት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው። እነርሱም በሰው ህይወት፣ አካልና ጤና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 538-579)፤ በሰው ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 580-606)፤ በሰው ክብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 607-619)፤ በመልካም ጸባይና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 620-661)፤ በንብረት መብት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች(ከአንቀጽ 662-733)፤ አለም አቀፍ ህግን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ዘርን ማጥፋት - አንቀጽ 269-280)፣ በመንግስት ገንዘብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ (የሀሰት ሰነድ ማዘጋጀት፣ የሀሰት ማህተም ማዘጋጀት፣ ገንዘብ ማዘጋጀት ...ወዘተ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሰዎች የንብረት መብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወንጀሎች ናቸው። ቀሪዎቹ ከ30 በመቶ የሚያንሱት ወንጀል ተብለው የተከለከሉት ድርጊቶች በመንግስት ተቋማትና መዋቅሮች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው። (ከአንቀጽ 238-268) በመንግሥት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ (ከአንቀጽ 284-342) ወታደራዊ ወንጀሎች እና በመከላከያ ሠራዊትና በፖሊስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ (ከአንቀጽ 402-465) በመንግሥት ሥራ ላይ አደራን በማፍረስ የሚፈጸሙ በስልጣን አላግባብ መገልገል

ወንጀሎች እና በፍትህ አስተዳደር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው፡፡ እነዚህም በጠቅላላው 149 አንቀጾች ናቸው፡፡

እነዚህ ወንጀሎች የነዋሪውን ሰብአዊ መብት ለማክበርና ለማስከበር በተቋቋሙ፣ ሰብአዊ መብትን የሚጥሱ ድርጊቶች ተፈጽመው ሲገኙ ደግሞ ለመመርመር፣ ለመክሰስና ለመዳኘት በተቋቋሙ የመንግስት መዋቅሮች፣ አደረጃጀቶችና አሠራሩ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው፡፡ እነዚህን የወንጀል ድርጊቶች በመንግስት ተቋማትና አደረጃጀቶች ላይ መፈጸም የመጨረሻ መጨረሻ የሰዎችን ሰብአዊ መብት ለመጣስ የሚያመች ሁኔታን መፍጠር ማለት ነው፡፡ የሰዎችን ሕይወት፣ ነጻነትና ንብረት ለመጠበቅ የተቋቋሙ መዋቅሮችን፣ አደረጃጀቶችንና የተዘረጉ ሥርዓቶችንና አሠራሮችን ማጥቃት ማለት የሰብአዊ መብት ጥበቃ አጥሩን፣ ከለላውን ማፍረስ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በመንግስት ላይ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚቃጡ ጥቃቶች ግባቸውና ዓላማቸው መንግስት የሰዎችን መብት የማስጠበቅ ስራውን ማስተጓጎል ስለሚሆን ነው፡፡

ስለሆነም የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የመጨረሻ ዓላማው ወንጀል ተብለው የተከለከሉት ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ መከላከል፣ እነዚህ የተከለከሉ ድርጊቶች ተፈጽመው በሚገኙበት ጊዜ ከምርመራ ጀምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተዘረጋው የስነስርአት ህግ መሰረት ወንጀል አድራጊው ከንጹሀን ተለይቶ እንዲቀጣ፣ቅጣት ከተጣለ በኋላ የቅጣት አፈጻጸም በህጉ መሰረት እንዲሆን በመከታተል የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ መጠበቅ ነው ቢባል ተገቢ ነው ማለት ነው፡፡

የፍትህ አካላት የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር በአጠቃላይ ፍትህን የማስፈን ስራ የሚለካባቸው አራት መመዘኛዎች ከዚህ በታች የቀረቡት ናቸው፡፡

1. **ውጤታማነት፣** ዜጎች ወይም ነዋሪዎች ወደፍትህ አካል ሲመጡ ትክክለኛ ውሳኔ በህጉ መሰረት ይሰጣል ብለው ተማምነው ነው፡፡ ውጤታማ ፍትህ ማለት በህግና በፍሬነገር ላይ ተመስርቶ በህጉ የሚጠበቀውን ደረጃውን የጠበቀ ፍትህ መስጠት ማለት ነው፡፡ በአጭሩ ፍትህ ማለት የሰዎች ሰብአዊ መብት እንዲከበርና እንዳይጣስ፣ ተጥሶ ከተገኘም ተገቢው ማስተካከያ እና ካሳ እንዲያገኙ ማድረግ ማለት ነው፡፡
2. **ቅልጥፍና፣** ዜጎች ፍትህን በአግባቡ ቢያገኙም ከሚገባው ጊዜ በላይ ከዘገየ ያው የዘገየ ፍትህ እንደተከለከለ ይቆጠራል እንደማለት ነው፡፡ ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ ክቡር ዶ/ር ከበደ

ሚካኤል ‹ጽጌረዳና ዳመና› በምትለው የግጥም ጽሁፋቸው የሚከተለውን ታሪክ እናገኛለን፡፡ ‹በጸሀይ ንዳድ ልትደርቅ የደረሰችው ጽጌረዳ ደመናን ዝናብ እንዲያዘንብላት ጠየቀችው፡፡ ደመና ግን ቆይ አሁን የምደርስበት አለ፣ ስመለስ አዘንብልሻለሁ ብሎ ጥሏት ሄደ፡፡ ከሄደበት ጉዳዩን ጨርሶ እስኪመጣ ጽጌረዳዋ በጸሀዩ ብርታት ሞታ ደርቃ ጠበቀችው፡፡ ደመናው እንደደረሰ የተሸከመውን ሁሉ ጎርፍ አዘነበ፡፡ ይሁንና ጽጌረዳ ሞታ ስለነበረ ሊያተርፋት አልቻለም፡፡› ይህ ምሳሌ የዘገየ ፍትህ እንደተከለከለ ይቆጠራል የሚለው ብሂልን ያስታውሰናል፡፡

3. **ተደራሽነት፣** ፍትህ እውን ሊሆን የሚችለው በወጪም ሆነ በቦታ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል ከሆነ፣ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጡ ለተገልጋዩ በቀላሉ ሊገባው የሚችልና ሊጠቀምበት የሚችል ሲሆን ነው፡፡ በመካከለኛው ክፍለዘመን ሀይለኛ ገዢ ስለነበረው ጀንጅስክሀን የሚነገር ነገር አለ፡፡ በጀንጅስክሀን አገዛዝ ስር የነበረው ህዝብ በጀንጅስክሀን መንግስት ሰራተኞችና ሀላፊዎች በመጉላላቱና በመበደሉ፣ ህዝቡ ለታላቁ ጀንጅስክሀን፣ የመደብካቸው የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች በደሉን፣ የሚጠይቁን ክፍያና ጉቦ ማለቂያ የለውም፡፡ ስለሆነም ከእኛ የሚጠበቀውን ግዴታ አውቀን እንድንወጣና የማይገባንን እንዳንከፍል ህግ አውጣልን አሉት፡፡ ታላቁ ጀንጅስክሀንም በጠየቃችሁት መሰረት ህግ አወጣላችኋለሁ በማለት መብትና ግዴታቸውን የሚገልጽ ህግ በጽሁፍ አዘጋጀ፡፡ ይሁንና ጽሁፉ በድቃቅ ቃላቶች (ጥቃቅን) ከመጻፉ በተጨማሪ ርቀቱ ከመሬት በጣም ከፍ ባለ ማማ ላይ ሰቀለው፡፡ ሰዎች ግን በዚህ ርቀት በድቃቅ የተጻፉትን ቃላቶች አንብበው መረዳት እና መጠቀም አልቻሉም፡፡ ስለሆነም ህጉ ቢኖርም ሊጠቀሙበት አልቻሉም፡፡ ስለሆነም ተደራሽነት ዜጎች ህጉን የህግ ስርአቱን በቀላሉ ተረድተው፣ ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ አገልግሎቱን ማግኘትን የሚያመለክት ነው፡፡
4. **ተገማችነት፣** ዜጎች ወደፍትህ አካል ሲመጡ ምን ሊወሰን እንደሚችል ሊገምቱ ይገባል፡፡ ዛሬ የሚሰጠው ውሳኔ ነገ ከሚሰጠው ውሳኔ የሚቃረን ከሆነ፣ ዜጎች በፍትህ ስርአቱ እምነት ሊጥሉ አይችሉም፡፡

እንግዲህ ፍትህን ማስፈን ወይም ፍትህን ማምጣት ማለት ከዚህ በላይ የተገለጹትን ነገሮች ያሟላ ሲሆን ነው፡፡ፍትህን ለማስፈን ደግሞ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ሙያዊ ስነምግባርን በተላበሰ መልኩ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

የሙያ ስነምግባርን በርእስ ለያይቶ (ከፋፍሎ) ማቅረብ እንደሙያው አይነት ይለያያል፡፡ የፍትህ ዘርፉ ባለሙያዎች አንድ የሚያደርጋቸው ሰብአዊ መብቶችን ለማክበርና ለማስከበር የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ግብ የሚመሩ ናቸው ፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ስነምግባር ማለት በጎ እና ክፉ፣ ወይም ትክክለኛ እና ትክክለኛ ያልሆነ ባህርይን ወይም ጠባይን የሚያመለክት ወይም እነዚህን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የምንመራበት ደንብ፣ ህግ ወይም መመሪያ እንደሆነ፣ እሴትና መርሆ ማለትም ስነምግባር ስለሚያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ማለትም የስነምግባር መርሆ የማክበር የመጨረሻ ግብ ምን እንደሆነ፣ ተጠቃሚው ማን ሊሆን እንደሚገባው፣ የስነምግባር መርሆዎች እነዚህን መሰረታዊ ጥያቄዎችን ሊመልስ በሚችል መልኩ የሚቀረጹ ስለመሆኑ ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም ሙያ በትምህርት፣ በስልጠና ወይም ስራውን በመስራት በልምድ የሚገኝን ንድፈ-ሀሳባዊ እውቀት፣ ክህሎት ስለመሆኑ፣ የሙያ ስነምግባር ማለት ሙያው በራሱ እንዲተገበር የሚያስገድደውን የሙያው አባላቶች እንደባለሙያ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚያውቁትን የሙያው መርሆዎች እንደሆነ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም የፍትህ አካላት ተጠቃሚዎች/ተገልጋዮች እነማን እንደሆኑ እና የፍትህ አካላት ተጠቃሚዎች ከፍትህ አካላት የሚፈልጉት እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉት ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽነትና ተገማች ያለው ፍትህ እንደሆነ ተካቷል፡፡

### የምእራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

አስረጅ ናሙና አንድ

አቃቤ ህግ በሚመረምረው የምርመራ መዝገብ ከተገኙት ማስረጃዎቹ በጣም ጠቃሚውና አስፈላጊው ህግን በመጣስ የተገኙ መሆኑን ይረዳል፡፡ ከእነዚህ አንዱ ፖሊስ የብርበራ ፈቃድ ሳያገኝ በህገወጥ መንገድ ቤት ውስጥ ገብቶ ያገኘው መረጃ መሆኑን ይረዳል፡፡ ይህ ህገ ወጥ ተግባር ባይፈጸም ኖሮ፣ ማስረጃው አይገኝም ነበር፡፡ አቃቤ ህግ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጃ መኖሩን እያወቀ ማስረጃውን ይዞ ፍርድ ቤት ቀረበ፡፡?

1. ከላይ በቀረበው አስረጅ ናሙና አንድ መሰረት ይህ የአቃቤ ህግ ድርጊት ሊያስጠይቀው ይገባል ወይ? አቃቤ ህጉ ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል?
2. አቃቤ ህጎች እና ፖሊሶች(መርማሪዎች) የሙያ ስነምግባርን ባያከብሩ ምን ሊፈጠር ይችላል?
3. የሙያ ስነምግባርን ማክበር ከግል ስነምግባር ጋር እንዴት ሊጋጭ ይችላል?

# ክፍል ሁለት

## የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች  የስነምግባር መርሆዎች

### 2.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ

በዚህ ምዕራፍ ፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች ሙያዊ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ሊያከብሩዋቸው ስለሚገቡት የሙያ ስነምግባር መርሆዎች፣ ከስነምግባር መርሆዎቹ አንጻር ሊያከብሩዋቸው የሚገቡ ዝርዝር ግዴታዎችና ሀላፊነቶች፣ ሙያዊ ስነምግባርን የእለት ተእለት መመሪያዎች ለማድረግ ሊተገብሩት ስለሚገባ ተግባራቶችና የመርማሪዎችን እና አቃቢያነ ህጎች ስነምግባራዊ ግዴታ ተግባራዊ ለማድረግ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ተቋማዊ ድጋፎች በአጭሩ ይቀርባል፡፡

### 2.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

የሥልጠናው ተሳታፊዎች የዚህን ምእራፍ ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ❖ ሰልጣኞች የሙያ ሥነ-ምግባርን ተቋማዊ በማድረግ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ይከላከላሉ፡፡

#### 2.2.1. የምእራፉ ዝርዝር አላማዎች

ሰልጣኞች ይህንን ስልጠና ሲያጠናቅቁ፣

- የስነምግባር መርሆች ምንነትና መገለጫዎቹን ይዘረዝራሉ፡፡
- በአድሎአዊነት አለመስራት መገለጫዎቹን ይገልፃሉ፡፡
- የሙያ ብቃትና ትጋት መገለጫዎቹን ይጠቁማሉ፡፡
- የሀላፊነትና ተጠያቂነት ምንነትና በምሳሌ ያስቀምጣሉ፡፡
- የቅንነት መገለጫዎች ያስረዳሉ፡፡
- የሀቀኝነት መገለጫዎች ያብራራሉ፡፡
- የስነምግባር መርሆዎችን በእለት ተዕለት ስራቸው ይተግብራሉ፡፡

## 2.3. የስልጠናው ይዘት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡እነርሱም፡-

- ሙያዊ ሀላፊነትን መወጣት፣
- በአድሎአዊነት አለመስራት
- የሙያ ብቃትና ትጋት
- ሀላፊነትና ተጠያቂነት
- ቅንነት
- ሀቀኝነት
- ሙያዊ ስነምግባርን ለማዳበርና ለማጠናከር ባህርያዊ እና ተቋማዊ ድጋፎች

## 2.4. አቃቤ ህግ የሚፈጽመው ቃለመሀላ

ሕግ እንደ አንድ የሙያ ዘርፍ በታሪክ ቀደምትነት ካላቸው ሙያዎች መካከል የሚመደብ ነው፡፡ ታሪክ እንደሚያሳየን ከሆነ ሕግና የሕግ ሙያተኞች ከቀደምት ጊዜ ጀምሮ የተደራጁ ማህበረሰቦች ሁሉ ዓይነተኛ መገለጫ ሆነው መሰንበታቸውን ነው፡፡ አቃቤ ህጎች እንደማንኛውም የህግና ፍትህ አስከባሪነት የሚሸከሙት ሀላፊነትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአቃቤ ህግ ደግሞ በተለየ የሚኖርባቸው ሃላፊነት አለ፡፡ ይህ ሀላፊነታቸው ምንድነው? በፌዴራል የአቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 443/2011 አንቀጽ 10 ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ አቃቤ ህግ በዋና ጉባኤው ፊት ቀርቦ የሚፈጽመው ቃለ መሀላ እንደሚከተለው ተደንግጎ ይገኛል፡

‹እኔ --------- ለሀገሬ ታማኝ በመሆን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስትን፣ ሌሎች ህጎችን የኢትዮጵያን አለምአቀፍ ግዴታዎች ያለምንም ማመንታት ላከብርና ላስከብር፣ የፌዴራል መንግስት ሕጎችን በመፈጸም እና በማስፈጸም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ልሰራ፣ የስራ ድርሻዬን ህግ በሚደነግገው መሰረት በመፈጸም የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት ላከብርና ላስጠብቅ፣ የግል ጥቅም ሳልፈልግ ማንንም በመውደድ፣ በመጥላት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት አድልዎ ላላደርግ፣ በስራ ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘሁትን ምስጢር ከአገልግሎቴ መቋረጥ በኋላ እንኳን ቢሆን በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ላልገልጽ፣ በስራዬም ሆነ በግል ሕይወቴ የሙያዬን ክብር

ልጠብቅ፣ ማንኛውንም ተጽእኖ ሳልፈራ በሀቀኝነት፣በቅንነትና በትጋት ሀላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ›

አቃቤ ህጉ ሊመራባቸው የሚገቡ የስነምግባር መርሆዎች ሁሉ በዚህ ቃለመሀላ ውስጥ ተገልጸው እናገኛቸዋለን፡፡

## 2.5. የፖሊስ ተቋም አላማና ግብ

የፖሊስ ተቋም አላማና ግብ የሀገሪቱን ህገመንግስት፣ ህገመንግስታዊ ስርአቱንና ሌሎች ህጎችን በማክበርና በማስከበር እንዲሁም ህብረተሰቡን በወንጀል መከላከልና ምርመራ በማሳተፍ የህዝብንና የመንግስትን ሰላምና ደህንነት መጠበቅና ማረጋገጥ ነው(የፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ 720/2004)፡፡ ማለትም ህይወትና ንብረትን መጠበቅ፣ ንጹሀንን ከመታለል ተግባር፣ ደካሞች ከጉልበተኞች ማስፈራራት፣ ሰላማዊውን ከጉልበተኞች፣ የሰዎችን የነጻነት የእኩልነት እና ፍትህ የማግኘት መብት ማክበርና ማስከበር እንዲሁም ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ ንጹሀንን ከወንጀል እና ከሰብአዊ መብት ጥሰት በመጠበቅ የህግ የበላይነትን ማስከበር ነው፡፡

ፖሊሶች (መርማሪዎች) እንደማንኛውም የህግና ፍትህ አስከባሪነት የሚሸከሙት ሀላፊነትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደፖሊስ ደግሞ በተለየ የሚኖርባቸው ሃላፊነትን ለመወጣት ሊያከብሩዋቸው የሚገቡ የሙያ ስነምግባር መርሆዎችና ግዴታዎች አሉ፡፡

## 2.6. የፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቢያነ ህጎች የስነምግባር መርሆዎች

### 2.6.1. ሙያዊ ነፃነት

1. የፖሊስ(መርማሪዎች) እና አቃቢያነ ህጎች ሙያ ሙያዊ ነጻነት ያስፈልገዋል?
2. ፖሊሶች(መርማሪዎች) አቃቤ ህግ መቀበል የሌለበት ምን አይነት ትእዛዝ ሲሆን ነው?
3. ፖሊሶች(መርማሪዎች) አቃቤ ህግ የማይቀበለው ትእዛዝን በተመለከተ ሀላፊነቱን እስከምን ድረስ መሸከም አለበት?

የፖሊስ እና የአቃቤ ህግ ሙያዊ ነጻነት በሚል በመርህ ደረጃ የሚታወቅ የለም፡፡ ነገር ግን የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ላይ የተሰማራ ተቋም ከአስፈጻሚው አካል ተጽእኖ ነጻ በሆነ

መልኩ ሊደራጅ እንደሚገባ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውና ያጸደቀቻቸው የተባበሩት መንግስታት እና የአፍሪካ ህብረት የጸረ ሙስና ስምምነቶች ይደነግጋሉ፡፡[5] በቀድሞው የፌዴራል ፖሊስ አዋጅ ቁ. 313/1995 አንቀጽ 4(2) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በህግና በሙያው የሚኖረው ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል የሚል ድንጋጌ የነበረ ሲሆን በአሁን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የህግና የሙያ ነጻነት የሚለው ቀርቶ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል› የሚል ብቻ ነው፡፡

ይሁንና ይሄ ማለት ፖሊስነት ሙያ ስለሆነ ሙያው የሚጠይቀውን ግዴታ የማክበር እና የማስከበር ግዴታ የለበትም ማለት አይደለም፡፡የፖሊስ ስራና ተግባር የህግ የበላይነትን ማስጠበቅ እንጂ የበላይ ሀላፊዎች ፍላጎት ማስፈጸሚያ አይደለም፡፡[6]ፖሊስ ስራውን ሲሰራ ሕገመንግስቱን፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች እና ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት እንዳለበት በየፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(2)(ለ) በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ ስለሆነም በመንግስት እና በፖሊስ መካከል ያለው ግንኙነት በህግና በህግ ብቻ የሚገዛና የሚተዳደር ነው ማለት ነው፡፡ ህግ አውጪው ህግ ያወጣል፡፡ ህግ አስከባሪ የሆነው ፖሊስ ይሄንን ህግ አውጪ ያወጣውን ህግ ያስፈጽማል፡፡ ስለሆነም የፖሊስ ዋና ስራ ህግ አውጪው ያወጣውን የወንጀል ህግ በአግባቡ የተፈለገለትን ውጤት እንዲያመጣ መስራትና መስራት ብቻ ነው፡፡[7]

የወንጀል ህጉ የተመሰረተው ንጹሀንን ከወንጀለኞች ለመጠበቅ ስለሆነ ፖሊስ በተግባሩ ይህንን የወንጀል ሕጉን አላማና ግብ በሚያሳካ መልኩ መስራት አለበት ማለት ነው፡፡ፖሊስ ምርመራ ሲያደርግ፣ ማስረጃ ሲሰበስብ፣ ተጠርጣሪን ሲይዝ፣ የተጠርጣሪን ቃል ሲቀበል የምርመራ ሪፖርት ሲያዘጋጅ ሙያው በሚጠይቀው መሰረትእውነትን ለማውጣት ማለትም ወንጀል መፈጸሙን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም በወንጀሉ ተሳታፊ ነው ለማለት ማስረጃው የሚመለከተውን ተጠርጣሪ ብቻ ለህግ እንዲያቀርብ የማድረግ ስራን ብቻ መስራት አለበት ማለት ነው፡፡

[5]የተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ስምምነት አንቀጽ 6
[6]A THINNING BLUE LINE? POLICE INDEPENDENCE AND THE RULE OF LAW p.2
[7]ከላይ የተጠቀሰው ገ.3

ከዚህ አንጻር ፖሊስ የምርመራ ስራውን ሲሰራ ንጹሀንን ያላግባብ እንዲጎዱ ወይም ወንጀለኞችን ለመጥቀምና ለማስመለጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አግባብነት የሌላቸው የተለያዩ ውጫያዊና ውስጣዊ ተጽእኖዎች በመቋቋም ሙያዊ ግዴታውን መወጣት ሙያዊ ሀላፊነት አለበት ማለት ነው፡፡ አግባብነት የሌላቸው ጣልቃ ገብነቶች ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ፣ ከሚዲያ፣ ከተለያዩ አካላት ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ማንኛውም ፖሊስ/መርማሪ፣

1. ስልጣን ከሌላቸው የመንግስት አካላት፣ ከሚዲያ፣ ከጓደኛ ፖሊስ ወዘተ በሚቀርቡ ማባበያዎችና ማስፈራሪያዎች ሳይበገር ሙያዊ ሀላፊነቱን ባስጠበቀ መልኩ ስራውን መስራት፣
2. ሹመት ታገኛለህ፣ ጥቅማጥቅም እንድታገኝ እናደርግልሀለን ብለው ህገወጥ ተግባር እንዲሰሩ የሚገፋፉትን መቃወም እና መቋቋም፣
3. ከተለያዩ ወገኖች የምርመራው አቅጣጫ መስመሩን እንዲስት የሚያደርጉ ተጽእኖ አድራጊዎችን መቋቋም፣
4. በተለይ በሙስና ወንጀል ጉዳይ ስልጣን ያላቸው አካላት ተጽእኖ ስለሚያደርጉ ይህንን መቋቋም፣ሙያዊ ስነምግባራዊ ግዴታ አለበት፡፡

ይህ ማለት ግን ፖሊስ/መርማሪ ህጋዊ ትእዛዝ መቀበል የለበትም ማለት አይደለም፡፡ የፖሊስ ተቋም እንደአስፈጻሚው አካል የራሱ የስልጣን ተዋረድ አለው፡፡ በፖሊስ ተቋሙ ውስጥ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀላፊዎች አሉ፡፡ እነዚህ በተቋሙ ውስጥ ስራቸውን እንዲሰሩ በህግ የተሰጣቸው ስልጣን አለ፡፡ ስለሆነም ፖሊሱ/መርማሪው በህግ ለሌሎች ሀላፊ ፖሊሶች የተሰጣቸውን ስልጣን ማክበር አለበት፡፡ ከበላይ ሃላፊው የሚሰጠውን ማንኛውንም ህጋዊ ትእዛዝ መፈጸም ይኖርበታል (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(9)፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ፖሊሶች የሚሰሩበትን ተቋም ፖሊሲዎች፣መመሪያዎች፣ደንቦች እንዲሁም ህጋዊ ትእዛዞችን ማክበርና መፈጸም አለበት፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ እንደቀረበው ፖሊስ ከህግ ውጭ ያልሆነ ትእዛዝ ሊቀበል የሚችለው በስልጣን ተዋረድ ከበላይ ሀላፊዎቹ ከሆኑት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ካሉ የመንግስት ባለስልጣኖች የሚመጡ ትእዛዞችን የመቀበል ግዴታ ስለሌለበት፣ ከዚህ አንጻር ከሚመጡ ተጽእኖዎችና ጣልቃ ገብነቶችን ራሱን መከላከል ይገባዋል ማለት ነው፡፡በተቋሙ ውስጥ በስልጣን ተዋረድ የበላይ ሀላፊ የሆኑት ባለስልጣናትም ቢሆኑ ለመርማሪው ትዕዛዝ ሲሰጡ በህግ ከተሰጣቸው የስልጣን ገደባቸውን ሳይተላለፉ መሆን ይገባዋል፡፡

ፖሊስ ከበላይ ሃላፊዎቹ መቀበል የሌለበት ምን አይነት ትእዛዝ ሲሆን ነው? የማይቀበለው ትእዛዝን በተመለከተ ሀላፊነቱን እስከምን ድረስ መሸከም አለበት?

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ፖሊስ ህጋዊ ትእዛዝን መቀበል አለበት። ህገወጥ የሆኑ ትእዛዞችን ግን መቀበል የለበትም። ህገወጥ ትእዛዞችን ተቀብሎ ታዝዤ ነው ብሎ ከተጠያቂነት ማምለጥ አይችልም።

በወንጀል ህግ አንቀጽ 71- ሊቋቋመው በማይችለው መንገድ ፍጹም ተገድዶ ሊደርስበት ከነበረው ጉዳይ በማይበልጥ ሁኔታ ወንጀል ያደረገ ሰው ተገድዶ ባደረገው ወንጀል አይቀጣም ይላል።

በሌላ በኩል በወንጀል ህጉ አንቀጽ 74 ትእዛዝ ፈጻሚው ወንጀል መሆኑን እያወቀ መፈጸም የሚያስቀጣ እንደሆነ ይደነግጋል።

አንቀጽ 74-- የትእዛዝ ፈጻሚው ተጠያቂነት

1. ትእዛዝ ፈጻሚው ትእዛዙ ከህግ ውጭ መሆኑን፣ በተለይም አዛዡ ለማዘዝ ስልጣን የሌለው ወይም ድርጊቱ ወንጀል መሆኑን እያወቀ የፈጸመውም ድርጊት የነፍስ መግደል ወይም የቃጠሎ ወይም በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ወይም ደግሞ በአገር ደህንነትና በህብረተሰብ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ ወይም በአለም አቀፍ ሕግ ላይ የደረሰ ከባድ አደጋ ሲሆን በጥፋቱ ሀላፊ ሆኖ ይቀጣል።
2. ትእዛዝ ፈጻሚው ጥፋት ያደረገው በመንግስት ስራ ወይም የወታደር ስርአት አፈጻጸም ስነስርአት በሚያስገድደው ተግባር ሆኖ ትእዛዙን ለመቃወምና ለመከራከር ባለመቻሉ በቀጥታ ከመፈጸም በቀር ሌላ የተሻለ መንገድ ለማግኘት ባለመቻሉ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በግልጽ በተረዳ ጊዜ ቅጣቱን በሙሉ ሊያስቀርለት ይችላል።

ፖሊስ በብርበራ፣ ሰውን በመያዝ፣ የተጠርጣሪን ቃል በመቀበል የምስክርን ቃል በመቀበል ሰብአዊ ክብሩን በሚነካ እና ከህግ አግባብ ውጭ የሆነ ተግባር መፈጸም የወንጀል ተግባር ሆኖ እንደሚያስቀጣ በወንጀል ሕጉ ከአንቀጽ 422-424 ተደንግገዋል።

አንቀጽ 422(2) ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለመበርበር ወይም ለመያዝ በህግ ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም ተገቢ ከሆነው ሀይል በላይ ተጠቅሞ ወደሌላ ሰው ቤት ወይም ግቢ የገባ እንደሆነ ወይም በህግ ከታዘዘው ወይም ከተፈቀደው ስርአት ውጭ የሰውን ንብረት የበረበረ የያዘ የወሰደ እንደሆነ ከአምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና መቀጮ ይቀጣል።

አንቀጽ 423--- ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በህግ ከተመለከተው ውጭ ወይም ህጋዊ ስርአትና ጥንቃቄ ሳይከተል ሌላውን ሰው በመያዝ፣ በማሰር፣ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ነጻነቱን ያሳጣው እንደሆነ ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል።

አንቀጽ 424–(1) ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የመያዝ፣ የመጠበቅ፣ የመቆጣጠር፣ የማጀብ ወይም የመመርመር ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የተጠረጠረን፣ የተያዘን፣ በምስክርነት የቀረበን፣ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የተጠራን፣ ተይዞ በማረፊያ ቤት ወይም በእስር ቤት የተቀመጠን ወይም የእስራት ቅጣት በመፈጸም ላይ የሚገኝን ሰው አንድ መግለጫ እንዲሰጠውም ሆነ ጥፋቱን እንዲያምን ወይም ይህን የመሳሰለ ነገር እንዲገልጽለት ወይም በፈለገው መንገድ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የደለለው፣ የተሰፋ ቃል የሰጠው ያስፈራራው ወይም በዚህ ሰው ላይ አግባብነት የሌለው ወይም ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ የሆነ ወይም ለሰው ልጅ ክብር ወይም ለተሰጠው የስራ ስልጣን ተቃራኒ የሆነ ድርጊት የፈጸመበት እንደሆነ፣ በተለይም ድብደባ፣ የጭካኔ ተግባር፣ ወይም የአካል ወይም የመንፈስ ስቃይ ያደረሰበት እንደሆነ፣ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል። ድርጊቱ ተጨማሪ ወንጀል ባስከተለ ጊዜ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በተደራቢነት እንዳይፈጸም የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ አያግድም።

(2) ወንጀሉ የተፈጸመው በባለስልጣን ትእዛዝ እንደሆነ ይህው ባለስልጣን ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ አስራትና በመቀጮ ይቀጣል፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ ወንጀል ተብለው የተዘረዘሩትን ድርጊቶች እንዲፈጽሙ የበላይ ሀላፊ ሲያዛቸው ፖሊሶች/መርማሪዎች ትእዛዙን ለሰጠው ሰው ትእዛዙ ህገወጥ መሆኑን ትእዛዙን ሊያከብሩና ሊፈጽሙት የማይችሉ መሆኑን መግለጽ ይኖርባቸዋል።

ህብረተሰቡ ፖሊስ በህግና በህግ ብቻ ነው ብሎ እምነት እንዲጥልበት እና ይህም እምነት በህብረተሰቡ እንዲሰርጽ ያስፈልጋል። እንዲህ አይነት ስርጸት ማምጣት ከባድ ቢሆንም ይሁንና ፖሊስ ሙያዊ ሀላፊነቱን ከፖለቲካና ከሌሎች አይነት ተጽእኖዎች ነጻ በሆነ መልኩ በህግና በህግ መሰረት ብቻ የሚሰራ መሆኑ እየተደጋገመ ሲታይ ግን ህብረተሰቡ በፖሊስ ተቋም ላይ እምነት እያሳደረ እንዲሄድ ማድረጉ አይቀርም። ከዚህ ጎን ለጎን የፖሊስ ሙያዊ ሀላፊነት ምንነትና ወሰኑ እስከምን ድረስ እንደሆነ ህብረተሰቡን ማስተማርና ማሳወቅ ህብረተሰቡ የፖሊስ

የሙያ ሀላፊነት እንዲከበር ደጋፊ ሀይል እንዲሆን ስለሚያደርገው ፖሊስ ህብረተሰቡን የፖሊስን ሙያዊ ግዴታ በተመለከተ ማሳወቅና ማንቃት ይጠበቅበታል፡፡

የአቃቤ ህግ ቃለመሀላ ውስጥ እንደተመለከው ‹…….ማንኛውንም **ተጽእኖ ሳልፈራ በሀቀኝነት፣ ….** ሀላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ› በዚህ ደንብ አንቀጽ 15(1) ‹አቃቤ ህጎች **ከማናቸውም ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡** ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡›

አቃቤ ህግ ውሳኔ ሲሰጥ (የምርመራ መዝገብ ሲዘጋ፣ ክስ እንዲመሰረት ሲወስን፣ ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሲመልሰው) ሙያው በሚጠይቀው መሰረት በተሰበሰበው የፍሬነገር ማስረጃ እና አግባብ ባለው ህግ ላይ ብቻ ተመስርቶ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ማስረጃው ያረጋገጠው ፍሬነገር እና የሚጠቀሰው ህግ የተጣጣመ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡

አቃቤ ህጎች ወንጀለኛን ለፍርድ በማቅረብ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ፣ የንጹሀንን መብትም እንዳይጣስ የመጠበቅ ህጋዊ ሀላፊነት አለባቸው፡፡

በዚህ ረገድ የዐቃብያነ ሕግን ሚና ለመወሰን በተባበሩት መንግሥታት የወጣው መመሪያና በዐቃብያነ ሕግ ዓለምአቀፍ ማህበር የወጣው የተግባር መመሪያ ሁሉም ሀገራት የዐቃብያነ ሕግን ሙያዊ ነፃነት ለማስጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸውና ተጨባጭ ርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባቸው ያመለክታል፡፡

ዐቃብያነ ህግ የመክሰስ ውሳኔን ለመስጠት ወይም ክስን ላለመመስረት ለመወሰን ያላቸውን ስልጣን ሲጠቀሙ በህግና በቀረቡላቸው ፍሬ ነገሮች ላይ በመመስረት እንጂ ከየትኛውም አቅጣጫ በሚመጣ ተፅእኖ ወይም ግፊት መወሰን የለባቸውም፡፡ የአለም አቀፍ ዐቃብያነ ህግ ማህበር የተግባር መመሪያ አንቀፅ 2/1/ አቃቤ ህግ በውሳኔ አሰጣጣቸው ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን እንደሚገባቸው ያትታል፡፡

ይህ የጠቅላይ አቃቤ ህጉ ስልጣን በተዋረድ ስልጣንና ሀላፊነት ያላቸው አቃቤ ህጎችን ይመለከታል፡፡

አቃቤ ህግ የሙያ ነጻነትን የሚያረጋግጠው ከተለያዩ አቅጣጫዎች (የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከሚዲያ፣ ከጓደኛ አቃቤ ህግ፣ ከመርማሪ ወዘተ) ሊመጡ ከሚችሉ ተጽእኖዎች ነፃ ሲሆን ብቻ

ነው፡፡ በማባበያዎችና ማስፈራሪያዎች ሳይበገር ጣልቃ ገብነትን እንቢ ሲል፣ በፍርሀት ከመወሰን ሳይታቀብ ሲቀር ነው፡፡

አቃቤ ህጎች ውሳኔ ሲሰጡ፣ በጉዳዩ ላይ ስልጣን የሌለውን ሰው ወይም ጓደኛ አቃቤ ህጎችን ሊያማክሩ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ውሳኔው የራሳቸው ነው፡፡ ስለሆነም አቃቤ ህጎች የሚሰጡት ውሳኔ በነጻነት፣ ከፖለቲካዊ ተጽእኖና ጣልቃ ገብነት እንዲሁም ከማይገባ ፍርሀት፣ ወገናዊነት በነጻ መልኩ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

ይሁንና ይህ ማለት ግን አቃቤ ህጉ በማንኛውም ጉዳይ መመሪያና ትእዛዝ መቀበል የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ትእዛዝ የሚቀበለው ግን ከማን ነው? ምን አይነት ትእዛዝ ነው የሚቀበለው?

የአቃቤ ህግ ተቋም እንደአስፈጻሚው አካል የራሱ የስልጣን ተዋረድ አለው፡፡ በአቃቤ ህግ ተቋሙ ውስጥ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀላፊዎች አሉ፡፡ እነዚህ በተቋሙ ውስጥ ስራቸውን እንዲሰሩ በህግ መሰረት የተሰጣቸው ስልጣን አለ፡፡ እነዚህ በአቃቤ ህጉ ተቋም ውስጥ ያሉ የአቃቤ ህግ ባለሙያዎች ክስን በሚመለከት፣ ወይም የምርመራ መዝገብን በሚመለከት የሚሰጣቸው ስልጣን አለ፡፡ ስለሆነም አቃቤ ህጉ በህግ ለሌሎች ሀላፊ አቃቤ ህጎች የተሰጣቸውን ስልጣን ማክበር አለበት፡፡በፌዴራል አቃቤ ህጎች ደንብ ቁጥር 443 አንቀጽ 71(2) አቃቤ ህጉ ከቅርብ ሀላፊ ወይም ከበላይ ሀላፊው የሚሰጠው ትእዛዝ በግልጽ ከህግ ውጭ ካልሆነ በቀር እንደትእዛዙ መፈጸም አለበት፣ በማናቸውም አኳኋን የቅርብ ሀላፊ ወይም የበላይ ሃላፊ ለሚሰጠው ትእዛዝ ህጋዊነት ተጠያቂ ነው ይላል፡፡

ስለሆነም አቃቤ ህጉ ከህግ ውጭ ያልሆነ ትእዛዝ ሊቀበል የሚችለው ከበላይ ሀላፊ ከሆኑት አቃቤ ህጎች ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ካሉ የመንግስት ባለስልጣኖች የሚመጡ ትእዛዞችን፣ ጣልቃ ገብነቶችን ግን የመቀበል ግዴታ ስለሌለበት፣ ከዚህ አንጻር ከሚመጡ ተጽእኖዎችና ጣልቃ ገብነቶችን መከላከል ይገባዋል ማለት ነው፡፡

ይሁንና እነዚህም የአቃቤ ህግ ባለስልጣናት ለዐቃብያነ ህግ ክስ እንዲመሰርቱ ወይም እንዳይመሰርቱ ትዕዛዝ ሲሰጡ ስልጣናቸውን ስራ ላይ ማዋል የሚገባቸው በግልፅነት፣ ህጋዊ የስልጣን ገደባቸውን ሳይተላለፉ መሆን ይገባዋል፡፡[8]

የሙያ ነጻነት ስነምግባር የሚጠይቀው በህግ የሚደረስበት ማንኛውም ድምዳሜ ሁሉ በማስረጃ በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ መመስረት አለበት ነው፡፡ ስለሆነም አቃቤያነ ህግ ሙያው ከሚፈቅደው ስራ ውጭ እንዲሰሩ ሲታዘዙ፣ሙያዊ ነጻነት መርሆ በሚጠይቀው መሰረት መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

የቀረበላቸውን የወንጀል ምርመራ መዝገብ በሚመረምሩበት ወቅት ክስ ለመመስረት ወይም ላለመመስረት የሚያደርጉት ውሣኔ ሁሌም ቢሆን ተገማችነት ሊኖረው የሚገባና ከማስረጃዎች ምዘና አንፃር የሚያራምዷቸው አቋሞች እርስ በርሳቸው የማይቃረኑ መሆን አለበት፡፡

አቃቤ ህጎች ስልጣን ከሌላቸው የመንግስት አካላት፣ ከሚዲያ፣ ከጓደኛ አቃቤ ህግ፣ ወዘተ በሚቀርቡ ማባበያዎችና ማስፈራሪያዎች ሳይበገሩ ሙያዊ ነጻነታቸውን ባስጠበቀ መልኩ ስራቸውን መስራት አለባቸው፡፡

አቃቤ ህጎች ከመርማሪዎች ጋር ከሚኖራቸው የስራ ግንኙነት ጋር በተያያዘም በመርማሪው የማይገባ ተጽእኖ (ማለትም መርማሪውን ለማስደሰት ወይም ቅር እንዳይለው፣ ወይም የስራ ግንኙነታችን ይበላሻል በማለት) ተመርተው እንዳይወስኑ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡

### 2.6.2. በአድሎአዊነት አለመስራት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. የተዛባ አመለካከት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በአድሎአዊነት አለመስራት ማለት ምን ማለት ነው?

ፖሊሶች እና አቃቤ ህጎች ወንጀለኛን ለፍርድ በማቅረብ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ፣ የንጹሀንን መብትም እንዳይጣስ የመጠበቅ ህጋዊ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ፖሊሶች ወገንተኝነታቸው ለህግ የበላይነትና ለሰብአዊ መብቶች መከበርና መከበር

[8] Standards of professional responsibility and statement of the essential dities and rights of prosecutors adopted by the international association of prosecutors on the twenty third day of April 1999 አንቀፅ 2/2/ እና /3/ ይመልከቱ፡፡

ብቻ ነው፡፡ እንኳንስ ቃለመሀላ እንደገባ ፖሊስ ይቅርና እንደሰውም ቢሆን አንድ ሰው ያላግባብ እንዲጎዳ መፈለግ በራሱ ለሞራል ተቃራኒና ነውር ነው፡፡ ማንም ሰውስ ቢሆን ያላግባብ ለምን ይጎዳል? ለምን ያላግባብስ ይጠቀማል?

ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በፍርድ ጥፋተኛ ነው ተብሎ እስካልተወሰነበት ድረስ በተቻለ መጠን እንደንጹህ የህብረተሰቡ አካል ስለሚቆጠር ሰብአዊ መብቱ አላግባብ እንዳይጣስ ፖሊስ እና አቃቤ ህግ መስራት አለበት፡፡

የፖሊስ ተግባራትን በመፈጸም ረገድ (1) ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት መፈጸም ወይም (2) በዘር፣ በብሄር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ልዩነት ማድረግ አይፈቀድም(አንቀጽ 14-- ፌዴራል ፖሊስ አዋጅ)፡፡ በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት (ሀ) በብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መካከል በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በቀለም፣ በፖለቲካዊ አመለካከት በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት አድልዎ ሳያደርግ ህጋዊ መብታቸውን የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት አለበት (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ 44(1)(ሀ)፡፡ በወንጀል ከተሳተፉት ውስጥ አንዱን መርምሮ ሌላውን ማስቀረት መድልዎ ነው፡፡

አቃቤ ህግ በዘር፣ በጾታ፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወዘተ… የተነሳ ከተጠርጣሪዎች ተከሳሾች መርማሪዎች ሌሎች የህግ ባለሙያዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት መድልዎ ማድረግ የለበትም፡፡

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ስነስርአታዊ ፍትህን ከማክበር አንጻርም (1) በተጠርጣሪዎች በኩል ያለውን ታሪክ የመሰማት መብት (2) ህግ በማስከበር ጊዜ ሰብአዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ ማከናወን (3) ገለልተኝነት- ማለትም ከተዛባ አመለካከት የጸዳ እና እምነት ሊጣልበት የሚችል አያያዝና ውሳኔ ሊኖር ይገባል፡፡

**የተዛባ አመለካከት ማለት ምን ማለት ነው?**

የተዛባ አመለካከት በሁለት መልኩ ሊገለጥ ይችላል፡፡ በእንግሊዝኛ Bias እና prejudice ይባላል፡ ፡

የተዛባ አመለካከት ማለት አንድን ሰው፣ አንድን ቡድን ወይም ዘር በቂ ማስረጃ ሳይኖር በጭፍን መደገፍ ወይም በጭፍን መቃወም ነው፡፡ በጭፍን መቃወም ሲባል በጭፍን መደገፍ ደግሞ ይባላል፡፡[9]ይህም በአጭሩ ጉዳዩን ቀድሞ ባለውስጣዊ እምነትና አመለካከት ወስኖ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ‹ነጋዴ ሲባል አጭበርባሪ ነው፡፡› ‹ሀይማኖተኛ ከሆነ ሊዋሽ አይችልም› ወዘተ…አይነት አመለካከቶች ናቸው፡፡ የተዛባ አመለካከት ያለው ሰው ማለት ማስረጃ ቢቀርብለትም አንዴ የያዘውን አቋም አልቀይርም ብሎ የሚቀጥል ነው፡፡

ፖሊስ በወንጀል ምርመራ ጊዜ በተጠርጣሪነት የተያዙ ሰዎችን ምስክሮችን ሲያስተናግዱም ሆነ ቃል ሲቀበሉ ተገቢውን ክብር መስጠታቸውን በሚያሳይ መልኩ እንጂ ተጠርጣሪውን ወይም ምስክሩን በሚያንቋሽሽ ወይም በሚያዋርድ አገላለፅ ወይም ቋንቋ፣ መጠቀም፣ የሽሙጥ ሳቅ የመሳሰሉት ተገቢ ያልሆኑ ባህርያትን ከማሳየት መቆጠብ አለባቸው፡፡ፖሊስ በሚወስነው ውሳኔ በወንጀል ሰለባው ላይ ሊደርስ ስለሚችለው በቅድሚያ ማሰብና መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የእነሱንም አስተያየትና ፍላጎት ከግምት ባስገባ መልኩ ይሁንና ከወገናዊነት በጸዳ ውሳኔውን መስጠት ይኖርበታል፡፡

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ የተዛባ አመለካከት ሰለባ እንዳይሆን ሁልጊዜም በንቃት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን የባህልና የማህበራዊ እሴቶች ለውጥን መከታተል ይገባዋል፡፡

አቃቤ ህግ ተከሳሹን ወይም ምስክርን ለማጥላላት ለመዝለፍ ወይም ለማስከፋት የታቀዱ አስተያየቶችን መስጠት ወይም ጥያቄዎችን መጠየቅ የለበትም፡፡አቃቤ ህግ አጠቃላይ ህብረተሰቡን ወክሎ ስለሚንቀሳቀስ፣ አንድ የግል ጠበቃ ለሚወክላቸው ተገልጋዮች እንደሚያደርገው የወንጀል ተጎጂውን ብቻ ለመደገፍ እንዲንቀሳቀስ አይጠበቅበትም፡፡ ይህ ማለት ግን ጨርሶውኑ የወንጀል ሰለባዎችን ተጎጂዎችን አይመልከት ማለት አይደለም፡፡ በሚወስነው ውሳኔ በወንጀል ሰለባው ላይ ሊደርስ ስለሚችለው በቅድሚያ ማሰብና መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የእነሱንም አስተያየትና ፍላጎት ከግምት ባስገባ መልኩ ይሁንና ከወገናዊነት በጸዳ ውሳኔውን መስጠት ይኖርበታል፡፡

ተከሳሾች ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመዳኘት መብታቸው እንዲከበር ተገቢውን ጥረት ማድረግ የሚኖርበት ሲሆን፣ ለተከሳሾች ጠቀሜታ ያለው ማስረጃ በእጁ በሚገባበት ወቅትም

[9]google- internet / Standards of professional responsibility and statement of the essential dities and rights of prosecutors adopted by the international association of prosecutors on the twenty third day of April 1999

እነዚህኑ ማስረጃዎች በተገቢው የሕግ ሥነሥርዓት መሰረት ለተከሳሾች መስጠት ይጠበቅበታል፡ ፡ ምክንያቱም ዐቃብያነ ሕግ ለፍትህና እውነት ነው መቆም ያለበት እንጂ ተከሳሹን መርታትን እንደ ሙያ ግብ አድርጎ መመልከት አይኖርበትም፡፡ ተከሳሽን የሚጠቅሙ ምስክሮችን ማንነት ለተከሳሽ መግለጽ ይኖርበታል፡፡ በቅጣት አወሳሰን ጊዜም ቢሆን ተከሳሹን በተመለከተ ቅጣቱን ሊያቀሉ የሚችሉ ምክንያቶች ከአሉ የመግለጽ ሙያዊ ሀላፊነት አለበት፡፡

በአጠቃላይ ፖሊስ እና አቃቤ ህግ፡-

1. የተጠርጣሪ የዋስትና መብት አላግባብ እንዲከለከል ማድረግ የለበትም፡፡
2. ምስክሮች የሀሰት ማስረጃ እንዲሰጡ ከማግባባትና ከማስፈራራት ሊቆጠብ ይገባል፡፡
3. ለጉዳዮ በምስክርነት መቅረብ የሚገባው ሰው ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ከማባበል ሊቆጠብ ይገባል፡፡
4. ተቃራኒ ወገን ማስረጃ እንዳያገኝ ማንኛውንም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሰል አድራጎት እንዲፈፅሙ መሞከር ወይም መርዳት የለበትም፡፡
5. ማንኛውንም ሰው ለተቃራኒ ወገን የምስክርነት ቃሉን ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ እንዳይሰጥ መገፋፋት የለበትም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ፖሊስ ገለልተኛነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ከሚያስገቡ ተግባራት መቆጠብ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር

1. ፖሊስ ልዩነትን በዘር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ ብሄራዊ ማንነት እና ሌሎችን መሰረት አድርገው መሰረታዊ መብቶችን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ከሚሰሩ ድርጅቶች አባልነት እራሱን ማራቅ፣
2. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል አለመሆን፣ ወይም የፖለቲካ ፓርቲን በመደገፍ ወይም በመቃወም ከመንቀሳቀስ መቆጠብ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(31)፣
3. የፖሊስ ስራን ከማስተዋወቅ ውጪ የተለያዩ የግል ተቋማትን ድርጅቶችን ማስታወቂያ ከመስራት ተግባር መቆጠብ፣
4. ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ፖሊሶች የቅስቀሳ ሰነድ ወይም ሌላ ምልክት በማንኛውም የፖሊስ ተቋም ህንጻ ወይም ተሽከርከሪ ላይ ከመለጠፍ መቆጠብ፣
5. የፖለቲካ አላማ ለማሳካት ገንዘብ ከመሰብሰብ ተግባር መቆጠብ፣
6. ለእጩዎች፣ ፓርቲዎች ወዘተ ፊርማ እና መዋጮ ከማሰባሰብ መቆጠብ፣

7. በምርጫ ጊዜ ጣልቃ በመግባት አንዱን የፖለቲካ ፓርቲ በሚጠቅም ወይም በሚጎዳ መልኩ ከመሳተፍ መቆጠብ፣
8. በፖለቲካ እምነቱ አንድ ሰው ስራ እንዲያገኝ ወይም እንዳያገኝ ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው፡፡

አቃቤ ህጉ ልዩነትን በዘር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ ብሄራዊ ማንንት እና ሌሎችን መሰረት አድርገው መሰረታዊ መብቶችን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ከሚሰሩ ድርጅቶች አባልነት እራሱን ማራቅ አለበት፡፡

የፌዴራል አቃቤ ህግ ደንብ አንቀጽ 71 ላይ የሚከተለው ተደንግጓል፡-
አቃቤያነ ህግ የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይም በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሳተፍ ወይም በስራቸው ላይ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን መግለጽ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ማሳየት የተከለከለ ነው፡፡በማናቸውም ሁኔታ በስራቸው ላይ የግል እምነታቸውን ወይም ሃይማኖታቸውን የሚያንጸባርቅ ተግባር መፈጸም የለባቸውም፡፡

ዐቃቢያነ ህግ ስራቸውን ያለ አድሎ ለማከናወን ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

1. ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት እንዲኖር የተጠርጣሪውን ንፅህና ወይም ጥፋተኝነት በሚመለከት ተገቢው ምርመራ እንዲካሄድና የምርመራውም ውጤት ይፋ እንዲደረግ የማድረግ፣
2. በህግና ርትዕ መሰረት በተከሳሹ፣ በተጎጂውና በህብረተሰቡ መካከል ፍርድ ቤቶች ትክክለኛውን ፍትህ እንዲያደርጉና እውነትን እንዲያፈላልጉ ተገቢውን ጥረት ማድረግና ፍርድ ቤቶችን መርዳት፣

የክሱ ማስረጃ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የተሰበሰበ እንደሆነ ወይም የተከሳሹን መሰረታዊ መብቶች በመጣስ የተሰበሰበ ማስረጃ እንደሆነ የዚህ አይነቱ ማስረጃ ለሚቀርበው ክስ በማስረጃነት እንዲያገለግል ማድረግ የማይገባ ሲሆን የተከሳሹን መብቶች በመጣስ ማስረጃውን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲሰበስብ ባደረጉ አካላት ላይ ተገቢውን ማጣራት ተካሂዶ ለህግ እንዲቀርቡ ማድረግ የዐቃብያነ ህግ ግዴታ ነው፡፡

## ~~2.6.3.~~ የሙያ ብቃትና ትጋት

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. የፖሊስ (መርማሪዎች) እና አቃቤ ህግ ሙያ ታታሪነትና የሙያ ብቃት እንዴት ይገለጻል?
2. ከፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ አባላት ምን አይነት የሙያ ብቃት ይጠበቃል?

አቃቤ ህግ በሚፈጽመው ቃለመሀላ የሚከተለው ይገኛል፡፡ ‹....የስራ ድርሻዬን ህግ በሚደነግገው መሰረት በመፈጸም የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት ላከብርና ላስጠብቅ...... በትጋት ሀላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ›

ደንብ ቁጥር 443/2011 አንቀጽ 4 በአቃቤ ህግነት ለመሾም የሚያበቁ ሁኔታዎች ተብለው ከተጠቀሱት መስፈርቶች ውስጥ፣ 1) በህግ ትምህርት የተመረቀ፣ 2) በታታሪነቱ በታማኝነቱ በፍትህዊነቱና በስነምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ ሊሆን እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡

የአገሪቱ ዜጋና ነዋሪዎች ከሁሉም በላይ በመጀመሪያ ከፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ ተቋም የሚፈልጉት እምነታቸውን የሚጥሉበት ተቋም እንዲሆን ነው፡፡ ዜጋውና ነዋሪው በፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ ተቋም ላይ እምነት ከሌላቸው በፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ የሚሰሩ ስራዎችን ሁሉ በጥርጣሬ የሚመለከቱት ሲሆን አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ከመስጠት እንዲቆጠቡ ያደርጋቸዋል፡፡ መብታቸውን ህጋዊ በሆነ መንገድ ከማስከበር ይልቅ ወደህገወጥ መንገድ ሊገፋፋቸው ይችላል፡፡ ከፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ ህብረተሰቡ እምነት እንዲጥልበት ህዝቡ የሚፈልገውን አገልግሎት በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና የፖሊስ ተቋም እና ከአቃቤ ህግ ማለት ሌላ ሳይሆን በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የተቋሙ ባለስልጣኖችና ሰራተኞች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፖሊስ እና ከአቃቤ ህግ ተቋማት አገልግሎቱን በጥራትና በጊዜ ሊያቀርብ የሚችለው በፖሊስ አባላቶቹ አማካይነት ነው፡፡

ስለሆነም ከፖሊስ እና ከ አቃቤ ህግ ታታሪነትና ትጋት እንዲሁም ሁልጊዜም አቅማቸውን ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡

ታታሪነት ማለት ሙያው በሚጠይቀው መሰረት ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ስራውን በሚፈለገው ጥራትና በቅልጥፍና በወቅቱ ማጠናቀቅን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር፡-

1. የተመደበበትን መደበኛ ስራ እውቀትና ችሎታውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም መፈጸም (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(8)፣
2. ስራውን በማስተዋል፣ በትህትና፣ በታጋሽነት እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ማከናወን (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ 44(2)፣
3. ተገልጋይን በአክብሮትና በትህትና ማስተናገድ፣ተገልጋዮች ሳይጉላሉ ጉዳያቸውን በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ተስተናግደው እንዲሄዱ ማድረግ(ፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 53(13)፣
4. መርማሪው የምርመራ ሪፖርት ከማቅረቡ በፊት ሁሉም መሰራት ያለባቸው ስራዎች መሰራታቸውን ሁሉም ሊሰበሰቡ የሚችሉ መረጃዎች መሰባሰባቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዷ የምርመራው ሰነድ ላይ ያለች ማስረጃና ማብራሪያዎች በተጎጂ፣ በምስክሮች እንዲሁም በተከሳሾች ላይ የሚያስከትሉት ውጤት ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም የምርመራ ስራው የማስረጃ ማሰባሰብ ስራውን በከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት መሰራት አለበት፡፡
5. ፖሊስ ሁልጊዜም ቶሎ ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ዝግጁ ሆኖ መቆየት አለበት፡፡እናም ፖሊስ በስራ ላይ እያለ ከመተኛት፣ ወይም የግል ስራውን ከመስራት ወይም ስራውን ሊያስረሱና ሀሳቡን ሊበታትኑ ከሚችሉ ሌሎች ተግባራቶች መቆጠብ አለበት፡፡

ይህንን በማድረጉ ጥራት ባለውና በተቀላጠፈ መልኩ ስራውን ስለሚሰራ ህብረተሰቡ በፖሊስ ተቋም አገልግሎት ይረካል፣ ስለሆነም በየፖሊስ ተቋም ላይ እምነት ያሳድራል፡፡

ትጋትና ታታሪነት ምናልባትም የስነምግባር መርሆዎች ማእከል ሊባል ይችላል፡፡ ዋና ትኩረቱንና የስራ ጊዜውን በአግባቡ ለተመደበበት ስራው የማያውል ፖሊስ ጉዳዮችን በማጓተት ወይም በጥንቃቄ ባለመመልከት ዜጎች እንዲጉላሉ፣ ፍትህም እንዲዛባ ያደርጋል፡፡ የፍርድ ቤት ትእዛዝን ባለማክበር የፍርድ ስራን እንዲስተጓጎል ያደርጋል(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(13)፡፡

የፌዴራል ፖሊስ ደንብ ማንኛውም ምልምል ፖሊስ በፖሊስ አባልነት ከመቀጠሩ በፊት መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና መውሰድና የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ እንዳለበት(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 5)፣ እንዲሁም ማንኛውም የፖሊስ አባል

ለተመደበበት ስራ ብቁ የሚያደርግ በመደበኛ ስራ ላይ ወይም ውጪ ሆኖ የሚሰጥ ስልጠና እንዲያገኝ እንደሚደረግ (ፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 11) ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን እውቀቱና ችሎታውን ማሳደግ በተቋሙ በሚሰጥ ስልጠና ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን የለበትም፡፡ውጤታማና ከስህተት የጸዳ ወይም ስህተቱ ያነሰ ስራ ለመስራት ሁልጊዜም ቢሆን እውቀትንና ክህሎትን ለማሳደግ መጣርና መትጋት ያስፈልጋል፡፡ ያወቅኩት ይበቃኛል ሳይሆን ሁልጊዜም እውቀቱንም ሆነ ክህሎቱን ለማዳበር መስራት ያስፈልጋል፡፡ በየጊዜው አቅሙን ለማጎልበት በሚሰጡ ስልጠናዎች ንቁ ሆኖ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡[10] በቴክኒካዊ እውቀት ላይ ብቻ ሳይመሰረት፣ ወሳኝ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዩች ላይ ሰፋ ያለ ዕውቀትና መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡ችሎታና አቅም የሌለው ፖሊስ ምንም ቅን ቢሆንም እንኳን፣ በችሎታ ማነስ ፍትህን ሊያዛባ ይችላል፡፡

ባለሙያው በየጊዜው እውቀቱንና ክህሎቱን በማዳበሩ፣

1) እራሱን ለከፍተኛ ሀላፊነቶች ዝግጁ ማድረግ ይችላል፣ የስራ አማራጩንም ማስፋት ይችላል፣ ተፈላጊነቱም ይጨምራል፡፡

2) ስራውን በጥራትና በጊዜ ሙያው በሚፈልገው ደረጃ በመስራቱ ህሊናዊ እርካታንም ያገኛል፡፡ ስለሆነም እንደፖሊስ እንዳትሳሳት በተቻለ መጠን እውቀትህንና ክህሎትህን አሳድግ፡፡ እንዳትሳሳት አትስነፍ፡፡ በደንብ አድርገህ የምርመራ ስራህን ስራ፡፡ አንተ በሌሎች በእውቀት እና ክህሎት ግድፈትና ስንፍና እንድትጎዳ እንደማትፈልገው ሁሉ፣ ሌሎችም በአንተ ስንፍናና ድክመት እንዳይጎዱ ሁልጊዜም ቢሆን ታታሪና አቅምህን በየጊዜው የምታዳብር ሁን፡፡

የስራ ሰአትን በማክበር ለሌሎች አርአያ ሁን (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ 44(4)፡፡

1. የመንግስት የስራ ሰአት በሙሉ ለመንግስት ስራ ከዋለ፣አገልግሎቶች በተፈለገው ጊዜ ለተገልጋዩ ይደርሳሉ፡፡ይህ ማለት ግን የግድ ቢሮ ውስጥ መቀመጥ ማለት አይደለም፡፡ ስራው በቢሮ ውስጥ ወይም ከቢሮ ውጭ ሊሰራ ይችላል፡፡ይሁንና የተቀጠረበትን ሙሉ ሰአት ለስራው ማዋል ይገባዋል ማለት ነው፡፡ ፖሊሶች ሁልጊዜ በስራቸው ላይ ስለመገኘታቸው ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡ በወቅቱ በስራው ላይ መገኘት የማይችሉ ከሆነ ለቅርብ አለቃቸው ማሳወቅ አለባቸው፡፡ የፖሊስ ባልደረባ የስራ ጊዜውን

[10] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.9

ለመንግስት ስራ ብቻ በማዋሉ ከሚሰማው ህሊናዊ እርካታ በተጨማሪ ወር ደርሶ ደመወዝ ሲቀበል፣ ያልሰራበትን ሳይሆን የሰራበትን ደመወዝ ሲቀበል የስራው ውጤት በመሆኑ ይደሰታል፣ ነጻነት ይሰማዋል። አለበለዚያ ግን ሳይሰራ የሚከፈለው ከሆነ ጥገኛ ነው ማለት ነው። ደመወዙ ከየትም ሳይሆን ከህዝብ በግብር መልክ የተሰበሰበ ስለሚሆን የህዝብ ሀብትና ገንዘብ መዝባሪ ይሆናል ማለት ነው። በስራውና በጥረቱ የሚኖር ሳይሆን፣ለእራሱ መኖር የማይችል ጥገኛ ይሆናል ማለት ነው።

2. በትርፍ ጊዜ ከሚሰራው ስራ ይልቅ ቅድሚያ ለፖሊስ ስራ ማዋል አለበት። ፖሊስ በትርፍ ጊዜ የሚሰራው ስራ የፖሊስነት ስራውን የሚያስተጓጉል ቢሆን ቅድሚያ ለፖሊስ ስራው በመስጠት እራሱን ተጨማሪ ስራ ከመስራት ማግለል አለበት።ፖሊስ በትርፍ ጊዜያቸው ሌሎች ስራዎችን በማከናወን ገቢ የሚያገኙ እንደሆነ ይህ ሁኔታ ተፈታትኗቸው ለመደበኛ ስራቸው ትኩረት እንዲነፍጉ ሊያደርግ ይችላል። ከዚህም አልፎ ፖሊሶች የያዙትን ከፍተኛ ኃላፊነት ወደ ጎን ትተው ገቢያቸውን ማዳበር ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ። ስለሆነም ሙሉ በሙሉ ሌላ የገቢ ምንጭ የሚያስገኝ ስራ አትስሩ ባይባልም፣ የፖሊስነት ስራ የህዝብ አገልጋይነት መሆኑን በመገንዘብ ፖሊሶች በመደበኛ ስራቸው ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫናዎችን ከሚፈጥሩባቸው ሌሎች ስራዎች ራሳቸውን ማግለል ወይም መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል።

አቃቤ ህግ ሀላፊነቱን በተጠያቂነትና በሀላፊነት ስሜት ለመወጣት ታታሪና ትጉህ እንዲሆን፣ እውቀቱንና ክህሎቱን ሁልጊዜም ለማዳበር የሚሰራ እንዲሆን ይጠበቅበታል።

በአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 69--- ስለታማኝነት በሚለው ርእስ ስር የሚከተሉት ተደነግገው እናገኛለን። (1) አቃቤያነ ህግ በስራ ነጻነታቸው የተጣለባቸውን እምነት መጠበቅ አለባቸው። (2) ማንኛውም አቃቤ ህግ መላ ጉልበቱን፣ ሀሳቡንና ችሎታውን በታማኝነት ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት ጥቅም ማዋል አለበት።

ውጤታማና ከስህተት የጸዳ ወይም ስህተቱ ያነሰ ስራ ለመስራት ሁልጊዜም ቢሆን እውቀትንና ክህሎትን ለማሳደግ መጣርና መትጋት ያስፈልጋል። ያወቅኩት ይበቃኛል ሳይሆን ሁልጊዜም እውቀቱንም ሆነ ክህሎቱን ለማዳበር መስራት ያስፈልጋል። በየጊዜው አቅሙን ለማጎልበት በሚሰጡ ስልጠናዎች ንቁ ሆኖ መሳተፍ ይኖርበታል። በቴክኒካዊ እውቀት ላይ ብቻ ሳይመሰረት፣ ወሳኝ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዩች ላይ ሰፋ ያለ ዕውቀትና መረጃ ሊኖረው ይገባል።

ችሎታና አቅም የሌለው አቃቤ ህግ ምንም ቅን ቢሆንም እንኳን፣ በችሎታ ማነስ ፍትህን ሊያዛባ ይችላል፡፡ ባለሙያው በየጊዜው እውቀቱንና ክህሎቱን በማዳበሩ፡-

1) እራሱን ለከፍተኛ ሀላፊነቶች ዝግጁ ማድረግ ይችላል፣ የስራ አማራጩንም ማስፋት ይችላል፣ ተፈላጊነቱም ይጨምራል፡፡

2) ስራውን በጥራትና በጊዜ ሙያው በሚፈልገው ደረጃ በመስራቱ ህሊናዊ እርካታንም ያገኛል፡፡

እንደአቃቤ ህግ እንዳትሳሳት በተቻለ መጠን እውቀትህንና ክህሎትህን አሳድግ፡፡ እንዳትሳሳት አትስነፍ፡፡ በደንብ አድርገህ መርምረህ ወስን፡፡ አንተ በሌሎች በእውቀት እና ክህሎት ግድፈትና ስንፍና እንድትጎዳ እንደማትፈልገው ሁሉ፣ ሌሎችም በአንተ ስንፍናና ድክመት እንዳይጎዱ ሁልጊዜም ቢሆን ታታሪና አቅምህን በየጊዜው የምታዳብር ሁን፡፡ በተለይም፣

1. አቃቤ ህግ ለመርማሪዎች በሚፈልጉት ጊዜና ወቅት አስፈላጊውን የሙያ ምክርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ እስከተቻለ ድረስ የማስረጃ ችግሮችን በወቅቱ በማረም አስፈላጊ ከሆነም ምርመራው ሳይንዛዛና ረጅም ጊዜ ሳይወስድ እንዲቋረጥም ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
2. የሚቀርብለትን የምርመራ መዝገብ በቂ ማስረጃ የለውም ብሎ ከመዝጋቱ በፊት በጥንቃቄ መመርመር፣ ከመርማሪው ጋር በመመካከርም መወሰን ምናልባት ያልተሟሉ ማስረጃዎች ከአሉ መርማሪው እንዲያቀርብ እድል መስጠት ይኖርበታል፡፡
3. ክስ ለመመስረት መወሰን ከባድ ውሳኔ ነው፡፡ ህግና ስርአትን ለመጠበቅና ለማስከበር ውጤታማ የሆነ የወንጀል ክስ መመስረት ተገቢ ነው፡፡ እያንዳንዷ የወንጀል ጉዳይ ክስ በተጎጂ፣ በምስክሮች እንዲሁም በተከሳሾቸ ላይ የሚያስከትሉት ውጤት ቀላል አይደለም፡፡ ስለሆነም አቃቤ ህግ ክስ ለመመስረት የሚሰጠው ውሳኔ በጥንቃቄና በትጋት መሆን አለበት፡፡ በአወጣው ያውጣው ወይም ፍርድ ቤት የሚያደርገውን ያድርግ በማለት አግባብነት የሌለውን አንቀጽ በመጥቀስ ተከሳሾች እንዲጉላሉ ከማድረግና የመንግስትን ሀብትና ጊዜ ከማባከን ተግባር ሊቆጠብ ይገባል፡፡

አቃቤ ህግ የምርመራ መዝገብን ሲዘጋ፣ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሲያዝ፣ ክስን ሲመሰርት፣ በክርክር ሂደት ክሱ እንዲሻሻል ሲጠይቅ ወይም ክሱ እንዲቆም ሲያደርግ ተገቢውን ምክንያት አግባብ ባለው ሕግ አስደግፎ ማተት አለበት፡፡

አቃቤ ህግ በትርፍ ጊዜ የሚሰራው ስራ የአቃቤ ህግነት ስራውን የሚያስተጓጉል ቢሆን ቅድሚያ ለአቃቤ ህግነት ስራው በመስጠት እራሱን ተጨማሪ ስራ ከመስራት ማግለል አለበት፡፡ በፌዴራል የአቃቤ ህጎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 80(ለ) የሚከተለውን እናገኛለን፡፡‹ለመስሪያ ቤቱ የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ለተሰጠው ስራና ሀላፊነት ተቃራኒ የሆነ ወይም ከስራውና ከሀላፊነቱ ወይም ከሙያ ስነምግባር ጋር የማይጣጣም ማንኛውንም የውጭ ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡›

### 2.6.4. ሀላፊነትና ተጠያቂነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. ፖሊሶች(መርማሪዎች) እና አቃቤያነ ህጎች ያለባቸው ኃላፊነት እና ተጠያቂነትን በተመለከተ ዘርዝሩ?

ማናችንም ሰዎች ንብረታችንን ወይም ልጃችንን አደራ ብለን እንዲያስተዳድር ሃላፊነት የሰጠነው ሰው ችግር ሲያጋጥም እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲል ብቻ በንብረታችን ላይ ወይም በልጃችን ላይ ጉዳት እንዲያደርስ አንፈልግም፡፡ ህዝብም ለፖሊስ እና አቃቤ ህግ አደራ ሲሰጥ ተጠያቂነትን የሚሸሽ ሳይሆን ተጠያቂነትን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡

የምንሰራቸው ስራዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሰዎች ላይ አሉታዊም ጉዳት ሊያመጡ ስለሚችሉ በተጠያቂነት መንፈስ በጥንቃቄ መስራትን ይጠይቃል፡፡ስራዎችን በንዝህላልነት እና በግዴለሽነት ሰርተን በኋላ ችግር ሲፈጠር ከተጠያቂነት መሸሽ፣ እኔ አይደለሁም ብሎ ወደሌላ ማሳበብ የተጠያቂነት መሰረታዊ ስነምግባራዊ መርሆን መጣስ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር፡-

1. ከተጠያቂነት በመሸሽ ሀላፊነቱን ወደሌላ በማዞር ሌሎችን ያለጥፋታቸው ጉዳት እንዲደርስባቸው የሚያደርግ ሳይሆን፣ የሚወስናቸው ውሳኔዎች እና የሚሰራቸው ስራዎችን በሀላፊነት እና በተጠያቂነት መንፈስ መስራት፣
2. መልካም አድርጎ ለመሸለም እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ስህተት ሲፈጽም ስህተቱን ተቀብሎ የሚመጣውን ለመቀበል ዝግጁ መሆን፣
3. ህግ፣ ስርአትና መመሪያ በሚያዘው መሰረት ወቅቱን ጠብቆ ስለሰራቸው ስራዎች፣ ያልተሰሩ ስራዎች፣ ስላጋጠሙ ችግሮች ተገቢውንና ትክክለኛውን ሪፖርት ማቅረብ፣

4. በሀላፊነትና በእምነት ስለሚሰራቸው ስራዎች የሚመለከተው አካል ሲጠይቅ (በምስጢር ሊጠበቁ ከሚገባቸው በስተቀር) በግልጽነት ያልተዛባ መረጃዎችና ማብራሪያዎችን መስጠት፣

ሀላፊነትን በተጠያቂነት መንፈስ አለመወጣት ቅጣትን ያስከትላል፡፡ የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 51(1) ማንኛውም የፖሊስ አባል ህግን በመጣስ በሚወስነው ውሳኔ ወይም በሚፈጽመው ድርጊት ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል ይላል፡፡

### 2.6.5. ቅንነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የቅንነት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

የቅንነት መርህ የሚያመለክተው ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በተመደቡበት የስራ ቦታ የተሰጣቸውን አደራና ሀላፊነት አከብራለሁ እጠብቃለሁ፣ የተሰጠኝን አደራና ሀላፊነት ለታቀደለት አላማና ግብ ብቻ ለማዋል እንጂ ለግሌ ወይም ለሌሎች ሰዎች ጥቅም አላውለውም ብሎ በግልጽም ይሁን ግልጽ ባልሆነ መንገድ የገቡትን ቃል ማክበርን የሚመለከት ነው፡፡

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በስራቸው ጊዜም ሆነ ከስራቸው ውጭ ስልጣንን እና ሀላፊነታቸውን ለለአግባብ ለግላቸው ወይም ለሌሎች ወገኖች ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ ከጀመሩ ማህበረሰቡም እምነት አይጥልባቸውም ፣ በወንጀል መከላከልና ምርመራ ስራቸውም አይተባበራቸውም፡፡
ስለሆነም ፖሊስ እና አቃቤ ህግ፡-

1. በሀላፊነት በተሰጠው ስልጣንም ሆነ ሀብት ቃሉን በማክበር የሚከተሉትን እንዲያደርግ ይጠበቃል፡፡

1.1. በእጁ የገባውን ወይም ለህዝብ ጥቅም እንዲያስተዳድረው በአደራ የተሰጠውን ሀብትና ንብረት በአግባቡ ለታቀደለት አላማ ብቻ ማዋልና መጠበቅ፡፡ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ከማዋል፣ ከመውሰድ፣ ከመጠቀም መታቀብ፡፡ በፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 46 ማንኛውም የፖሊስ አባል ለስራ የተሰጠውን የመንግስት ሀብት በአግባቡ የመጠበቅና ለታቀደለት አላማ ብቻ የመጠቀም ሀላፊነት አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡

1.2. በህግ ማስከበር ስራ ጊዜ በእጁ የገባውን ንብረት፣ጠፍቶ የተገኘ ንብረት ወዘተ ለግል ጥቅም ከማዋል በመቆጠብ በአግባቡ ለሚመለከተው አካል ማስረከብ፣

1.3. የተቋሙን ወይም የባለጉዳይን ሰነዶችን፣ሪከርዶችን ማስረጃዎችን በአግባቡ መጠበቅ፣ ከመደለዝ፣አስመስሎ ከማዘጋጀት፣ ማጥፋት፣ መደበቅ፣ ማበላሸትና መቀየር መቆጠብ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(28)፣

1.4. በስራ አጋጣሚ ያወቀውን ምስጢር ለምርመራ እና የፖሊስ ህግ ማስከበር ስራ አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በማናቸውም ሌሎች ፍላጎቶችን ለማሟላት ከመጠቀም መቆጠብ(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(27)፣ በአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 74 ምስጢር ስለመጠበቅ በሚለው ውስጥ፣ ማንኛውም አቃቤ ህግ መረጃው ተራ ወይም በህዝብ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ወይም መደበኛ ስራውን በህጋዊ መንገድ ለመፈጸም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በስራው አጋጣሚ ወይም ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘውን መረጃ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ወይም ሀላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ በስተቀር በአሰራር ምስጢር የተባሉትን መረጃዎች፣ ቃለጉባኤዎች፣ የስራ እቅዶችና እነዚህን የመሳሰሉትን ምስጢራዊ ጉዳዮች ሁሉ በስራም ላይ ሆነ ከስራ ውጭ ለሌላ ማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም፡፡› በማለት ይደነግጋል፡፡

1.5. ስልጣን ባለው ሀላፊ ካልታዘዘ ወይም ከስራው ባህሪ አንጻር ጉዳዩን እንዲያውቀው የሚገባው ሰው ካልሆነ በስተቀር የፖሊስን የስራ እንቅስቃሴ፣ ስምሪት፣ ትጥቅና ተመሳሳይ መረጃዎችን ለማይመለከተው ሰው አለመግለጽ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(6)፣

1.6. በተገቢው አካል ሳይወከል ስለመስሪያ ቤቱ ጉዳዮች ለመገናኛ ብዙሀን መግለጫ ከመስጠት መቆጠብ(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(10)፣

1.7. የማይገባ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት በምስጢር የተያዙ የወንጀል ምርመራ ውጤቶችን ከመሸጥ መቆጠብ፣

1.8. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በስራ አጋጣሚ ከሚገናኙ ተገልጋዮችም ሆነ ማናቸውም ሰዎች ጋር በሰዎቹ ሰብእና ላይ ጉዳት ከሚያደርስ የቋንቋ አጠቃቀም እና ባህርይ መቆጠብ፡፡ ማንኛውም የፖሊስ አባል ህጻናትን፣ ሴቶችን፣ አረጋውያንንና የአካል ጉዳተኞችን ስሜታቸውን በማይነካ ሁኔታ በእንክብካቤ የመያዝ ግዴታ አለበት (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 50)፡፡

1.9. የፖሊስ ሀይል ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝነት ያልሆነ ሀይል ከመጠቀም መቆጠብ፡፡ በፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 45 እንደተደነገገው

የፖሊስ አባል ሀላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት ግልጽ ተቃውሞ ካጋጠመውና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ተመጣጣኝ የሆነ ሀይል ሊጠቀም ይችላል፡፡ የፖሊስ አባል በዚህ መሰረት የጦር መሳሪያ ሊጠቀም የሚችለው (ሀ) በራሱ ወይም በሌላ ሰው ላይ ሞት ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ከሚያደርስ ጥቃት ለመከላከል፣ (ለ) በማምለጥ ላይ ያለ አደገኛ የወንጀል ተጠርጣሪ በህግ ቁጥጥር ስር ለማዋል ወይም ከእስር በማምለጥ ላይ ያለን ተጠርጣሪ ወይም ፍርደኛን ለማስቆም ከጦር መሳሪያ ውጭ ያሉ ሌሎች እርምጃዎች በቂ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ብቻ ነው፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች የጦር መሳሪያ የተጠቀመ የፖሊስ አባል (ሀ) ጉዳት የደረሰበት ሰው አስቸኳይ የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ እና (ለ) ስለተፈጠረው ሁኔታ ለሚመለከተው የበላይ ሀላፊ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

2. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ከስራው ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት ሲፈጥሩ ከሚችሉ የስራ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የፖሊስ እና የአቃቤ ህግ  ስራውን እንዳይጎዳ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር፣

2.1. ከራሱ፣ ከስጋ ዘመዱ ወይም ከጋብቻ ዘመዱ ጥቅም ጋር የተያያዘ እና ከስራ ሀላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጥርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው (ለምሳሌ ከራሱ ወይም የቤተሰብ ጉዳይ ወይም ቢዝነስ ጉዳይ ባለው ጉዳይ ምርመራ የተጀመረ ከሆነ) ለአለቃው በጽሁፍ የማሳወቅ እና የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ ከአለቃው በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ስራውን ማከናወን (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(7) እና የፌደራል አቃቤ ህጎች ደንብ አንቀጽ 77) ፡፡

ፍትሀ ነገስት እንዲህ ይላል፡፡‹**ለጠላቱ ሊፈርድለት አይገባም፣ ፈርቶኝ እንጂ ነው ይለዋልና፡፡ ሊፈርድበት አይገባም፣ በቀሉን እንጂ ሊወጣብኝ ነው ይለዋልና**›ማናቸውም አቃቤ ህግ የራሱ፣ የዘመዶቹ ወይም የወዳጆቹ የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከስራው ወይም በስራው ምክንያት ከያዘው የህዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ለቅርብ ሀላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ አቃቤ ህግ እንዲታይ ማመልከት አለበት፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ሀላፊም ጉዳዩ እውነት መሆኑን ካረጋገጠ ጉዳዩ በሌላ አቃቤ ህግ እንዲታይ ማድረግ አለበት፡፡

2.2. በምርመራ ስራው ላይ ከሚሳተፉ ወይም ከገቡ ምስጢራዊ መረጃ አቀባዮች፣ተጎጂዎች፣ ምስክሮች ጋር የፍቅር ግንኙነት ከመመስረት መቆጠብ፣

2.3. ማንኛውም የፖሊስ  እና አቃቤ ህግ አባል የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ከሙያ ግዴታው ጋር የሚጋጭ ወይም የማይጣጣም ማናቸውም ሌላ ስራ ከመስራት መቆጠብ እና በትርፍ ጊዜው ለሚሰራው ስራ ተቋሙን ማሳወቅ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 47 እና የፌደራል አቃቤ ህጎች ደንብ አንቀጽ 80 )

2.4. ከስራው ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሰጠው ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከማንኛውም ሰው ከመቀበል መቆጠብ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 47 እና የፌደራል አቃቤ ህጎች ደንብ አንቀጽ76 )፡፡

2.5. በወንጀል ምክንያት ሆነ በሌላ ጉዳይ ቢያዝ(arrested) ወይም ምርመራ የተጀመረበት መሆኑን ሲያውቅ  ወዲያውኑ ለቅርብ አለቃ ማሳወቅ፣

2.6. የፌዴራል የአቃቤ ህጎች መተዳደሪያ ደንብ ከዚህ አንጻር የሚከተሉት ድንጋጌዎችን እናገኛለን፡፡ አንቀጽ 75--- አዘውትሮ ገንዘብ መበደር የተከለከለ ነው፡፡ አቃቤ ህግ በስራው ምክንያት ከሚያጋጥመው ባለጉዳይ ገንዘብ ለመበደር መሞከር ወይም መበደር ፍጹም ክልክል ነው፡፡

2.7. በሚመለከተው የበላይ ሀላፊ ሳይፈቀድ ማንኛውንም መዋጮ ከመሰብሰብ መቆጠብ(ደንብ አንቀጽ 44(14)፡፡

3. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላው ለማስገኘት ስልጣኑንና ክብሩን መሳሪያ በማድረግ ከመጠቀም መቆጠብ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(12)፡፡ ከዚህ አንጻር ለምሳሌ፣

3.1. የትራፊክ ስርአት ጥሶ በፖሊስነቱ እና በአቃቤ ህግነቱ  ያገኘውን ስልጣን ከተጠያቂነት ነጻ ለመሆን ከመጠቀም መቆጠብ፣

3.2. ፖሊስ የግል ቢዝነሱን በሚያካሄድበት ወቅት የፖሊስነት ስልጣኑን በመጠቀም በመስሪያ ቤቱ ደብዳቤ በመጠቀም መልዕክቶችን ከመለዋወጥ መቆጠብ፣

3.3. አገልግሎት ፍለጋ የሆነ ቦታ ሄዶ ከቢሮክራሲያዊ አሰራሮች በማምለጥ በፍጥነት ለመስተናገድ ሲል ፖሊስ እና አቃቤ ህግ መሆኑን በመግለፅ በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገድ ከመጠየቅ መቆጠብ፣

3.4. የፖሊሱ እና አቃቤ ህግ ልጁ ወይም ባለቤቱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ቢታሰር ፖሊስነቱን እና አቃቤ ህግነቱ  በመጠቀም እነዚህ ሰዎች ከሌላው የተለየ መስተንግዶ ተደርጎላቸው እንዲፈቱ ወይም ጉዳያቸው በትኩረት እንዲታይ ግፊት ከመፍጠር መቆጠብ፣

3.5. የፖሊስነት እና የአቃቤ ህግነት ስልጣንን ጓደኛውን ለመጥቀም ወይም ጠላቱን ለመጉዳት ከመጠቀም መቆጠብ፣

3.6. መታወቂያቸውን፣ባጃቸውን፣ዩኒፎርማቸውን ላልተፈቀደለት ሰው ከመሥጠት ተግባር መቆጠብ፣

3.7. በአማላጅ አለመስራትና ራሱን በአማላጅነት አለመቅረብ (ፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(11)።ዳኞች በስሜት፣ በፍርሀት ወይም በተዛባ አመለካከት እንዲወስኑ ከመገፋፋት መቆጠብ።

4. ስነምግባር የለውም ተብሎ በሚገመት ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ማህበረሰቡ እምነት አይጥልበትም። በተቋሙ ላይም ጥርጣሬን በመውለድ እምነት እንዳይኖር ያደርጋል። ስለሆነም ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ስልጣኑን ለራሱ የግል ጥቅም ያውላል ወይም ለወዳጆቹ ጥቅም ያውላል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሊፈጥሩ ከሚችሉ ተግባራት መቆጠብ ይኖርበታል። ከዚህ አንጻር

4.1. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በችሎት ከሚከራከሩ ጠበቆች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በአግባቡ ደረጃውንና መጠኑን የጠበቀ ሊሆን ይገባል። ዳኞችን ከችሎት ውጪ በማግኘት ተከራካሪው ወገን በሌለበት በችሎት በተያዘ ጉዳይ ላይ ለማነጋገር ከመሞከር መቆጠብ፣

4.2. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ከፍያለ ስጦታ ወይም ከፍተኛ ወጪ ያለውን ግብዣ ከመቀበል መቆጠብ ይኖርበታል።የቤተሰብ አባላቱ ወይም የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች በእርሱ ስም ስጦታ ወይም ብድር እንዳይወስዱ ማስታወቅና ማሳሰብ አለበት።

### 2.6.6.ሀቀኝነት

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በግል አኗኗሩ የተቋሙን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንዳይከት መጠንቀቅ ይኖርበታል። ተቋሙ ተገቢውን ክብር፣ ድጋፍና ተአማኒነት የሚያገኘው ፖሊሱ በግል አኗኗሩ በሚያሳየው ባህርይ ነው።

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶችን የጣሱ ሰዎችን ለፍርድ የሚያቀርብ ከመሆኑ አንጻር እሱም እራሱ በድርጊቱ ሰብአዊ መብቶችንና ነጻነቶችን የሚያከብርና አርአያ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። በህገመንግስቱ እና በአለምአቀፍ የሰብአዊ መብት መግለጫዎችና

ስምምነቶች የተመለከቱትን ሰብአዊ መብቶች በማክበር በጽኑ መቆምና አርአያ ሆኖ መታየት ይኖርበታል፡፡

ሌሎች እንዲያከብሩት የምትፈልገውን ህግና ስርአት አንተም አክብር፡፡ አንተ እንዲሆን የምትፈልገውን ሌሎችም እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡ የአንተ ሰብአዊ መብት እንዲጣስ የማትፈልግ ከሆነ የሌሎችንም ሰብአዊ መብት አትጣስ፡፡ በአንተ ላይ የሚፈጸም ሰብአዊ መብት ጥሰት ሌሎች አይተው እንዳላዩ እንዳይሆኑ የምትፈልግ ከሆነ አንተም እንዳላየህ አትሁን ነው፡፡
የፌዴራል አቃቤ ህግ አስተዳደር ደንብ በአንቀጽ 70 ስለአቃቤ ህግ ጸባይ ስለእያንዳንዱ አቃቤ ህግ ጠባይ የሚከተለውን ደንግጎ እናገኛለን፡፡

1. ማንኛውም አቃቤ ህግ የህዝብን አክብሮትና እምነት እንዲያገኝ በመስሪያ ቤቱም ሆነ ከመስሪያ ቤቱ ውጭ በማናቸውም ጊዜ መልካም ጠባይና ስነምግባር እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡
2. በማንኛውም ጊዜ የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

አቃቤ ህግ በግል አኗኗሩ የተቋሙን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንዳይከት መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ ተቋሙ ተገቢውን ክብር፣ ድጋፍና ተአማኒነት የሚያገኘው አቃቤ ህጉ በግል አኗኗሩ በሚያሳየው ባህርይ ነው፡፡ ስለሆነም ህግ አስከባሪ በመሆን እምነት እንዲጣልበት ከማንም በላይ ህግ አክባሪ መሆን አለበት፡፡ በግል ህይወቱ ከማጭበርበር ውሸታም ከመሆንና ከመሳሰሉት መቆጠብ አለበት፡፡አቃቤ ህግ በክርክሩ ቢረታ፣በይግባኝ ወይም ቀጣይ ባለው ህጋዊ ስርአት መሰረት ለማስለወጥ ከመሞከር ውጭ ከፍርድ ቤት ውጭ የፍርድ ቤትን ውሳኔ አለአግባብ ከመተቸት መቆጠብ አለበት፡፡አቃቤ ህግ የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘ ጉዳይ ላይ መግለጫ ከመስጠት ወይም ጽሁፍ በማሳተም ፍርድ ቤቱን ከመተቸት መቆጠብ አለበት፡፡

አቃቤ ህግ የሌላውን አቃቤ ህግ ኢስነምግባራዊ ድርጊት አይቶ እንዳላየ ማለፍ የለበትም፡፡ ሌሎችን ህግን እንዲጥሱ መምከር ወይም ህግ ሲጥሱ ዝም ብሎ ማየት የለበትም፡፡

ይሁንና አቃቤ ህጉ አቃቤ ህጉ መብት እንደሌለው ተደርጎም መታየት የለበትም፡፡ አቃቤ ህጉ የፈጸመው ወይም ሊፈጽመው የተዘጋጀው ስራ እንደ ግለሰብ መብት በህግ የተጠበቀ ነው ወይ?

አቃቤ ህጉ ድርጊቱን ሲፈጽም ደረጃውን ያልጠበቀ እና ታማኝነቱን ጥርጣሬ የሚያስገባ ነው ወይ? እንደመስፈርት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ በአቃቤ ህጉ የተደረጉት ተግባራትን በጭፍኑ ከመቃወም በፊት፣

1. አቃቤ ህጉ ድርጊቱን ሲፈጽም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደረገ መሆኑ፣
2. በአቃቤ ህጉ ድርጊት ሌሎች ሰዎች የተጎዱ መሆኑ፣ ወይም በሌሎች ሰዎች እይታ እንደጉዳት የሚታይ መሆኑ፣
3. ድርጊቱ ለህብረተሰቡ ክብር የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ መሆኑ፣
4. የአቃቤ ህጉ ባህርይ በተጽእኖ (bias) የማይመራ መሆኑ፣
5. የአቃቤ ህጉን የተሟላ ሰብእና ያሟላ ወይም ያከበረ ለመሆኑ እንደመስፈርት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

በግል ህይወታቸው ፖሊሶች ደረጃውን የጠበቀ ባህርይ ማሳየት አለባቸው፡፡ ማለትም ፖሊሶች ሀቀኞች አይደሉም፣ሀሰተኞች ናቸው ሊያስብላቸው የሚችል ጥርጣሬ ከሚያነሳ ድርጊት ራሳቸውን ማቀብ አለባቸው፡፡ የሚሰሩበትን ተቋም ደረጃ ከሚቀንስ ከሚያዋርድ ተግባር መቆጠብ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር እያንዳንዱን ባህርይ ዘርዝሮ ማስቀመጥ ባይቻልም የተወሰኑ ማሳያዎችን ማስቀመጥ ግን ይቻላል፡፡

1. ከማንም በላይ ህግ አክባሪ መሆን አለበት፡፡ማንኛውንም አይነት የወንጀል ድርጊት በጽናት የመከላከል እና ራሱም ከወንጀል ድርጊት መራቅ አለበት (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44 (2)ሐ)፡፡
2. በስራ ቦታ ወይም ከስራ ቦታ ውጪ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(8)፡፡
3. በስራ ቦታ ወይም ከስራ ቦታ ውጪ ጾታዊ ጥቃት ከመፈጸም መቆጠብ(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(22)፡፡
4. በስራ ቦታም ሆነ ከስራ ቦታ ውጪ የስርቆት፣ የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ተግባር ከመፈጸም መቆጠብ(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 54(24)፡፡
5. ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ደረጃውን የጠበቀ ጓዳዊ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንዱ ለሌላው አርአያ መሆን ይገባቸዋል፡፡በስራ ላይ መጋጨት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እናም በቋንቋ አጠቃቀማቸውም ሌላውን ሰው ሞራሉን ሊጎዳ ከሚችል ቋንቋ አጠቃቀም ሊቆጠቡ ይገባል፡፡

6. የበላይ አመራርን ማክበር ይገባል (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 44(10)፡፡
7. መልካም ስነምግባርን የሚያጎድሉ አካባቢዎችን ባለማዘውተር የራሱን እና የተቋሙን ክብር መጠበቅ ይገባል (የፌዴራል ፖሊስ ደንብ 44(3)፡፡ የደንብ ልብሱን ለብሶ አልባሌ ቦታ ከመገኘት መቆጠብ ይገባል(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 53(9)፡፡
8. በሌላ የፖሊስ ባልደረባ የሚደረግን ህግን የመጣስ ወይም ኢስነምግባራዊ ድርጊትን (በራስ ህይወት ላይ አደጋ የማያስከትል ከሆነ) የማስቆም ወይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል(ለቅርብ አለቃ) ማሳወቅ ይገባል(የፌዴራል ፖሊስ ደንብ አንቀጽ 53(7)፡፡
9. በንደኞቻቸው ላይ በሚደረግ ምርመራ እውነተኛውን ማስረጃ የማቅረብ እና ከመዋሸት ማስረጃ ከመደበቅ መቆጠብ ይገባል፡፡

ፖሊስ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ለማንኛውም ሰው እውቅና የተሰጠው ሰብአዊ መብት አለው፡፡ በሰብአዊ መብቱ ሲጠቀምም እንዲህ ተጠቀም እንዲህ አታድርግ ሊባልም አይገባም፡፡ ነገር ግን ሰብአዊ መብት አጠቃቀሙ ከሙያ ግዴታው ጋር እንዳይጋጭ ሊጠነቀቅ ይገባል፡፡ ስለሆነም ማንኛውንም ድርጊት ከማድረጉ በፊት ትክክል ነው አይደለም ለማለት ከሚከተሉት ጥያቄዎች አንጻር ማየትን ይጠይቃል፡፡ እነሱም፣

1. ፖሊስ የፈጸመው ወይም ሊፈጽመው የተዘጋጀው ስራ እንደግለሰብ መብት በህግ የተጠበቀ ነው ወይ?
2. ፖሊሱ ድርጊቱን ሲፈጽም ደረጃውን ያልጠበቀ እና ታማኝነቱን ጥርጣሬ የሚያስገባ ነው ወይ? የሚሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ በፖሊስ የሚደረጉ ተግባራትን በጭፍኑ ከመቃወም በፊት፣

1. ፖሊስ ድርጊቱን ሲፈጽም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደረገ መሆኑ፣
2. በፖሊሱ ድርጊት ሌሎች ሰዎች የተጎዱ መሆኑ፣ ወይም በሌሎች ሰዎች እይታ እንደተጉዳት የሚታይ መሆኑ፣
3. ድርጊቱ ለህብረተሰቡ ክብር የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ መሆኑ፣

መመዘኛዎች መሰረት በማድረግ አንዳንድ ጊዜ አከራካሪ ሊሆኑ የሚችሉ ምርጫዎችን መወሰን ይገባል፡፡

## 2.7. ሙያዊ ስነምግባርን ለማዳበርና ለማጠናከር ባህርያዊ እና ተቋማዊ ድጋፎች

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. የስነምግባር መርሆዎችን የቀን ተቀን የስራ መመሪያና ባህሪ እንዴት ማድረግ እንችላለን?
2. አቃቤ ህግ በሚመረምረው በቂ ማስረጃ እንደሌለው በሚያውቀው መዝገብ ላይ ክስ መስርተህ ተከራከር የሚል የበላይ ትእዛዝ ቢመጣ ምን ማድረግ አለበት? እንዲህ አይነት ግንኙነት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ ምን አይነት ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል?

የስነምግባር መርሆዎችን ስላነበብናቸው ወይም ስላወቅናቸው ብቻ ተግባራዊ ይደረጋሉ ማለት አይደለም፡፡ ባህርያችን እንዲሆን፣ ጠባያችን እንዲሆን ማድረግ ይገባናል፡፡

ባህርይ ወይም ጠባይ ማለት በተደጋጋሚ በማድረጋችን ምክንያት በውስጣችን ተገንብቶ፣ መመራመርና መተንተን ሳያስፈልገን የቀን ተቀን ህይወታችንን የሚመራ የተዘጋጀ ስርአት ነው፡፡

በውስጣችን ያለውን ወደመጨረሻው ግብ የማያደርስን መልካም ያልሆነ ባህርይ በአንድ ጊዜ አውጥቶ ለመጣል ቀላል እንዳለመሆኑ ሁሉ፣ አዲስ ባህርይን ለመላበስም ቀላል አይደለም፡፡ ስለሆነም ፖሊሶች (መርማሪዎች) እና አቃቤ ህጎች በትክክለኛ የስነምግባር መርሆች የሚመራ ባህርይና ጠባይ እንዲኖራቸው ቢያንስ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ቁርጠኝነት ያስፈልጋል፡- የስነምግባር መርሆዎቹን መሰረት አድርገን በተደጋጋሚ ሳናወላዳ በመወሰን ባህርያችን ወይም ልማድ ልናደርገው ይገባል፡፡
- ተነሳሽነት ያስፈልጋል፡- የስነምግባር መርሆዎቹን መሰረት አድርገን በመወሰናችን ምክንያት በመጨረሻ የሚገኘው ጥቅም፣ ባለማድረጋችን የሚደርሰውን ጉዳት በየጊዜው ብናስታውስ እንዳንወድቅና እንዳንሰለች ያግዘናል፡፡ በአርአያነታቸው የምናያቸውን ሰዎች ታሪክ ወይም የህይወት ተሞክሮአቸውን በማንበብና በማስታወስ ልንደክም ስንል ያነሳሱናል፣ ብርታት ይሰጡናል፡፡
- ጓደኞቻችን {መምረጥ ያስፈልገናል፡- ተመሳሳይ የሆነ ዝንባሌና አመለካከት ያላቸው ሊሆን ይገባል፡፡ አብረህ የምትውላቸውን ጓደኞችህን ንገረኝ ማንነትህን እነግርሀለሁ እንደሚባለው ብሂል፡፡

### የፖሊሱን /መርማሪውን እና አቃቤ ህግን ስነምግባራዊ ባህርይን የሚደግፍ ተቋማዊ ድጋፎች

ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት ማለት በአንድ አገር የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈጻሚ፣ የህግ ተርጓሚ፣ ብዙሀን መገናኛ፣ ሲቪል ማህበረሰቡ እና በጠቅላላው በአገሪቱ የሚኖረው ነዋሪ ልማድና ባህል መካከል ያለውን የቁጥጥር መስተጋብርና የስርአቱን ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ለመመዘን የሚያገለግል ቻርት ሲሆን፣ በዚህ መልኩ የተለዩትን ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ለማጎልበት ስለሆነም የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርአትን ለማጠናከር ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ለማሳየት የሚረዳ ሞዴል/ቻርት ነው፡፡

ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት እና የባለሙያዎች የሙያ ስነምግባር ማክበር እርስ በርስ የሚደጋገፉ እንጂ አንዱ ብቻውን ውጤት የሚያመጣ አይደለም፡፡ ጠንካራ ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት ካለ የመንግስት ባለስልጣኖች ሊያስከትል የሚችለውን ተጠያቂነት በመገንዘብ የማይገባ ተግባር ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፣ እንዲሁም ጥሰቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ቀድሞ ወደነበረበት እንዲመለስ የማድረግ ሚና ያለው ነው፡፡

ይሁንና በዚህ ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት ውስጥ ስነምግባርን የሚተገብር ባለሙያ ከሌለበት ትርጉም የለውም፡፡ በሌላ በኩል የሌለው ወይም ደካማ ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት ባለበት፣ ስነምግባር የሌላቸው ሰዎች ስርአቱን ጨርሶ ለማፍረስ ለሚፈልጉ ምቹ ሁኔታ ሲሆን፣ ስነምግባርን ለሚያከብሩ ባለሙያዎች ስነምግባራቸውን ጠብቀው ለመስራት ከባድና አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቤ ህጎች ሙያዊ ስነምግባርን መተግበር ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ባልተናነሰ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ብሄራዊ የተጠያቂነት ስርአት እንዲዘረጋ፣ የተዘረጋው እየተጠናከረ እንዲሄድ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
በፖሊስ ተቋም ውስጥ ፖሊሶች (መርማሪዎች) እና በጠቅላይ አቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ውስጥ አቃቤ ህጎች የሙያ ስነምግባራቸውን ከባድ እና አስቸጋሪ ባልሆነ መልኩ ለመተግበር እንዲችሉ ደጋፊ ተቋማዊ ስርአቶች ሊኖሩ ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህ ተቋማዊ ስርአቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

1. መልካም ስነምግባር ያላቸውን ባለሙያዎች ሊያመጣ የሚችል፣ የስነምግባር ችግር ያለባቸውን ደግሞ ወደተቋሙ እንዳይመጡ ለመከላከል የሚያስችል የፖሊሶች የምልመላና የቅጥር ስርአት፣
2. ፖሊሶች (መርማሪዎች) እና አቃቤ ህጎች ሙያዊ ግዴታቸውን ያለ ማስፈራራት፣ እክል፣ ትንኮሳ፣ አግባብ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት፣ ወይም ለምክንያት አልባ የፍትሃብሄር፣ የወንጀል ወይም ሌላ ሃላፊነት ሳይጋለጡ ሀላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ የስራ ዋስትና የሚያረጋግጥ ስርአት ማለትም ከሀላፊነት የሚነሱበት፣ የሚዘዋወሩበት ሁኔታ ግልጽነት ያለውና በዘፈቀደ የማይነሱበት ስርአት መዘርጋት፣
3. የፖሊሶች (መርማሪዎች) እና አቃቤ ህጎች የአገልግሎት ሁኔታዎች፣ ደመወዝና የአገልግሎት ዘመን፣ ጡረታ ወዘተ ገለልተኝነታቸውንና ነፃነታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ማደራጀት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፖሊሶች (መርማሪዎች) እና አቃቤ ህጎች የሥራ ዕድገት በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በተመሰረተ ህግ በተለይም ሙያዊ ብቃትን፣ ችሎታን፣ ጠንካራ ስብዕናን፣ እና ልምድን መሰረት ያደረገ ፍትሃዊና ገለልተኛ የሆነ ስርዓት ተከትሎ እንዲወሰን ማድረግ፣

## ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ፖሊሶች/መርማሪዎች እና አቃቤ ህጎች ስለሚመሩባቸው የስነምግባር መርሆዎችና ዝርዝር የመርሆዎቹ አፈጻጸም ከፌዴራል ፖሊስ አዋጅ እና የፌዴራል ፖሊስ ደንብ ጋር በማነጻጸር ቀርበዋል፡፡በዚህም መሰረት የሙያ ሀላፊነትን መወጣት ማለት ሕገመንግስቱን፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች እና ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና የማስከበር እና በህግና በህግ መሰረት ብቻ መስራት ስለመሆኑ እና ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ በሆነ መንገድ መስራት ስለመሆኑ፣ የበላይ ሀላፊን ህጋዊ ትእዛዝ መቀበል ግዴታ ስለመሆኑ ነገር ግን ህገወጥ ትእዛዝን መቀበል የሌለበት ስለመሆኑ እና ህገወጥ ትእዛዝ ሊባሉ የሚገባቸው ምን እንደሆኑ፣ የገለልተኝነት መርህ ማለት  ማለት ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ለተጠርጣሪም ሆነ ለጠቅላላው ህዝብ በገለልተኝት የማገልገል ግዴታ ያለው ስለመሆኑ፣ በተግባሩ ከተዛባ አመለካከት የጸዳ ሊሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣ ሁልጊዜም ሙያዊ እውቀቱንና ችሎታውን ሊያሳድግ እንደሚገባው፣ በሚሰራው መልካም ስራ ለመሸለም እንደሚፈልግ ሁሉ ከተጠያቂነት በመሸሽ  ሳይሆን በተጠያቂነት መንፈስ መስራት እንደሚገባው፣ በቅንነት መርህ እየተመራ መስራት እንደሚገባው ማለትም ስልጣኑን ለግሉ ወይም ለሌሎች ወገኖች መጠቀሚያ ከማድረግ መቆጠብ የሚገባው ስለመሆኑ እንዲሁም በሀቀኝነት ማለትም ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ሌሎች ህግ እንዲያከብሩ ሲጠይቅ እሱም ህግ አክባሪ፣ ሰብአዊ መብት አክባሪ መሆን እንደሚገባው ከማንኛውም አይነት ወንጀል ውስጥ መገኘት እንደሌለበት ለመዳሰስ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ክፍል የፌዴራል ፖሊስ አዋጅ እና የፌዴራል ፖሊስ ደንብ  እና አቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ያሉ በርካታ ስነምግባርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አግባብነት ባለው ቦታ ሁሉ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የስነምግባር መርሆዎችን የራስ ባህርይ ለማድረግ ቁርጠኝነት፣ ተነሳሽነት ሊኖረው እንደሚገባ እንዲሁም አብሮ የሚውላቸው ጓደኞቹ መልካም ስነምግባርን እንዲያሳድግ የሚደግፉትን ሊሆን የሚገባው ስለመሆኑ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም ፖሊሱ/መርማሪው እና አቃቤ ህጉ  ሙያዊ ስነምግባሩን ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ የሚደግፉ እና የሚያጠናክሩ ተቋማዊ አሰራሮች መካከል የተወሰኑትን ማለትም በምልመላ፣ በስራ እድገት፣ በማዘዋወር ጋር በተያያዘ ሊተገበሩ የሚገባቸውን አሰራሮች ይጠቁማል፡፡

## የምዕራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### አስረጅ ናሙና አንድ

አንድ የምርመራ መዝገብ ተጠናቆ የመጣለት አቃቤ ህግ የተሰባሰቡትን ማስረጃዎች ሲመረምር አንዳንዱ ተከሳሽን የሚጠቅም ሆኖ ያገኘዋል። በጉዳዩ ላይ ክስ ከመመስረቱ በፊት የበላዩ ከሆነው አቃቤ ህግ ጋር በሚወያዩበት ጊዜ፣ ተከሳሹን የሚጠቅም ማስረጃ ተከሳሹ ቢያውቀው የአቃቤ ህጉን ክርክር እንደሚያከብድበት፣ ይሁንና ለተከሳሹ ማስረጃው መሰጠት እንደሚገባ፣ ሀሳቡን ይገልጻል። ይሁንና አለቃው ተከሳሽን የሚጠቅመው ማስረጃ በክሱ ውስጥ እንዳይጠቀስ እንዲሁም ለተከሳሹም ማስረጃው መሰጠት እንደሌለበት መመሪያ ይሰጠዋል።

### አስረጅ ናሙና ሁለት

በአንድ ወቅት የነበሩ አንድ ዳኛ በማጭበርበር የተከሰሱ የመንግስት ሰራተኞች ገና በክርክር ላይ እያሉ ፍርድ ቤት በቀጠሮ ቀን በቀረቡ ጊዜ ሁሉ ‹መንጋ ሌባ› ሁሉ እያሉ ይናገሩ ነበር።

1. ከላይ በቀረበው አስረጅ ናሙና አንድ መሰረት አቃቤ ህግ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?
2. ከላይ በቀረበው አስረጅ ናሙና ሁለት መሰረት የዳኛውን ድርጊት እና በውሳኔው ሊያመጣው የሚችለውን ችግር ዘርዝሩ?
3. በፖሊሶች (መርማሪዎች) እና አቃቢያነ ህጎች ከሙያ ስነምግባር በወጣ መልክ የሚፈጸሙ ስህተቶችን እና ጥፋቶችን ዘርዝሩ፣
4. በፖሊስ ተቋም ፖሊሶች(መርማሪዎች) እና አቃቢያነ ህጎች ያለስጋት የስነምግባር መርሆዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያሉትን ጠንካራ ሁኔታዎች እና በተቃራኒው የስጋት ምንጮች የሆኑ ተቋማዊ ችግሮች ምን እንደሆነ ይዘርዝሩ፣
5. በፖሊስ የምርመራ ስራ ለምሳሌ በማስረጃ አሰባሰብ፣ ከተጠርጣሪ ጋር በተገናኘ፣ ከምስክር ጋር በተገናኘ ከአድሎ በጸዳ መንገድ እንዳይሰራ ተጽእኖ ሊያደርጉ ይችላሉ ብላችሁ የምትገምቱዋቸውን የተዛባ አመለካከቶች አንስታችሁ ተወያዩበት።
6. መርማሪ በምርመራው ሂደት ተጠርጣሪውን የሚጠቅም ማስረጃ ቢያገኝ ለተጠርጣሪው እንዲሰጥ ይጠበቃል ወይስ ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል?

7. በቅጣት አወሳሰን ጊዜ ተከሳሹን በተመለከተ ቅጣቱን ሊያቀሉ የሚችሉ ምክንያቶች ከአሉ አቃቤ ህግ የመግለጽ ሙያዊ ሀላፊነት አለበት? ወይስ ሁልጊዜም ከፍተኛውን ቅጣት እንዲቀጣ መጠየቅ ነው?ይግባኝ ሁልጊዜ መጠየቅ ተገቢ ነው ወይ ?
8. ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ከጓደኞቻቸው ጠበቆች እና ዳኞች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? ከጠበቆች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ትክክል እና አግባብ የማይሆነው መቼ ነው? ከመገባበዝ ሊቆጠቡ ይገባል? ከጓደኛ ዳኞች ጋር ያላቸው ግንኙነት ትክክል የማይሆነው የትኛው ነው? ከዳኛ እና ከጠበቃ ጋር በቤተሰብ ግንኙነት ያላቸው ምን አይነት ጥንቃቄ ይጠበቃል?



## ማጣቀሻ ጽሁፎች/ዋቢዎች

### አዋጆችና ደንቦች ስራ ላይ በዋሉበት አመት ቅደም ተከተል


1. የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ 1949
2. የፍትሀ ብሄር ህግ 1952
3. የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ህግ 1954
4. የፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ 1958
5. የልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁ 8/1967
6. የልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ማሻሻያ  አዋጅ ቁጥር 214/1974
7. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁ. 1/1987
8. የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988
9. የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/1992
10. የፀረ-ሙስና ልዩ ሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/93
11. የፌዴራል ፖሊስ አዋጅ ቁ. 313/1995
12. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ 1996
13. የተሻሻለው የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97
14. የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97
15. ሀብትን ለማሳወቅና ለማስመዝገብ የወጣ አዋጅ ቁጥር 668/2002
16. የጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃና ከለላ አዋጅ ቁ. 699/2003
17. የፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ 720/2004
18. የፌዴራል ፖሊስ አባሎች መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 268/2005
19. የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006
20. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007
21. የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ማሻሻያ ቁ. 882/2007
22. የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁ. 943/2008
23. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
24. የፌዴራል የአቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 443/2011
25. የፌዴራል ፖሊስ የሙስና ወንጀል ...የክስና ጥቆማ አቀባበል ..... ማንዋል 2009

26.የኢትዮጵያ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ መመሪያ፣ 2011 ዓ.ም

27.የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1236/2013

**የታተሙና ያልታተሙ መጽሀፍቶች፣ የምርመር ጽሁፎች፣ የስልጠና ሰነዶች**

28. የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ (1993)
29. ፍትሃ ነገስት ንባቡ እና ትርጓሜው ፣ትንሳኤ የመፅሃፍት ማሳተሚያ ድርጅት(አዲስ አበባ 1990 ዓ.ም)
30. ጸሐይ ዋዳ፣ **<u>የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች</u>** (አዲስ አበባ 1994 አ.ም)
31. የስነምግባርና የጸረ ሙስና ሞጁሉች (2000)፣
32. በሪሁ ተክለብርሀን፣ **<u>ለዳኞችና አቃቤ ህጎች የተዘጋጀ የወንጀል ስነስርአት ስልጠና ማንዋል(የፍትህ አካላት የስልጠና ማእከል)</u>**(ያልታተመ)(2000)
33. መካሻ አበራ፣**<u>የአቃቤ ህግ የስነምግባር መርሆዎች ለውይይት የተዘጋጀ</u>**(ያልታተመ)(2012)
34. መስፍን ማሬ፣ **<u>የወንጀል ክስ አመራር በኢትዮጵያ</u>** (አዲስ አበባ 2013 አ.ም)
35. መካሻ አበራ እና አንሙት ላቀው፤ **<u>የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ የስልጠና ማንዋል ለማዘጋጀት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት</u>**(ያልታተመ) (2013)
36. ፊ.ስጸኮ፣ **<u>የሙያ ስነምግባር ምንነት</u>** (ያልታተመ)
37. የስነምግባር ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም ሰነድ ቅጽ 2(ያልታተመ)
38. ሰብአዊ መብትና የፖሊስ ሚና (ከፍትህ ለሁሉም የስልጠና ማንዋል)2004
39. የማስረጃ ህግ-- ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል(ያልታተመ)
40. የኢትዮጵያ ወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ማስተማሪያ ማንዋል (በፍትህ አካላት ስልጠና ማእከል)
41. ኑር ሰኢድ፤ **<u>የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ስነስርአት</u>**
42. AFRICAN UNION CONVENTION ON PREVENTING AND COMBATING CORRUPTION
43. Amercian Bar Association website (posted on September 2019
44. Attorneys Paul Bergman & Sara J. Berman-Barrettrepresent yourself in court (2003)
45. Bryan A. Garner(ed.), *Black's Law Dictionary*, (Washington: West Publishing Co., 8th ed ., 2004).
46. CODE OF CONDUCT FOR CROWN PROSECUTORS: November 28, 2006
47. Declaration of Independence 1775
48. Fundamentals of Criminal Law (internet accessed)

49. Graham Gooch and Michael Williams, 2014, **Oxford A dictionary of Law Enforcement** (1ed), 2007
50. Google- internet / Standards of professional responsibility and statement of the essential dities and rights of prosecutors adopted by the international association of prosecutors on the twenty third day of April 1999
51. Kahsay and Andualem; **law of evidence teaching material** Justice and Legal System Research Institute 2009
52. International Association of Prosecutors, Standards of professional responsibility and statement of the essential duties and rights of prosecutors, April 1999
53. John Stwart Mill, On Liberty 1859 (Batoche Books Kitchener (2001)
54. Lindy Muzila and others: **On the Take Criminalizing Illicit Enrichment to Fight Corruption** (2012)
55. Mizan Law Review, **The Preliminary Inquiry in Ethiopa and its Adverse Impact on the Rights of the Accused** (Wondwossen Demissie Kassa) (2020)
56. **OECD Corruption Investigation and Prosecution Training Manual** (2012)
57. Paul Mageean, Belfast, **The Role and Indepenedence of Prosecutors** Northern Ireland 17 th May 2005, Cairo
58. Philipe Graven, **An introduction to Ethiopian Penal Law** (1965)
59. **Proposed draft Evidence Code of the Federal Demorcatice Republic of Ethiopia** (prepared by the Faculty of Law of Jimma University, Jimma, Ethiopia)
60. Robert H.Aronson and Donald T.Weckstein, **Professional Responsibility in a Nutshell**,(2d,1991)
61. Robert Klitgaard; **A Holistic Approach to the Fight against Corruption;** Bali, Indonesia January 29, 2008
62. ROD GEHL AND DARRYL PLECAS; **Introduction to Criminal Investigaton-Processes- Practices-and- Thinking** (2016)
63. **The competence of supreme courts: the second meeting of central and Eastern European countries,** Council of Europe, 1998
64. **The Code for Crown Prosecutors.** 2004/www.cps.gov.UK (internet document)
65. THE GLOBAL PROGRAMME AGAINST CORRUPTION UN ANTI-CORRUPTION TOOLKIT 2004

66. THE JUDICIAL INTEGRITY GROUP, COMMENTARY ON THE BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT,2007
67. A THINNING BLUE LINE? POLICE INDEPENDENCE AND THE RULE OF LAW The Police Foundation John Harris Memorial Lecture, delivered by Shami Chakrabarti, Director of Liberty, on July 2, 2008
68. THE Works of Epictitus, translated from the Greek by Thomas Wentworth Higginson, 1890, Boston
69. Transparency International, Global Corruption Report 2007
70. UN BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT, 2006
71. UN Code of Conduct for Law Enforcement Officials,1979
72. UN Guidelines on the Role of Prosecutors,1990
73. UNITED NATIONS CONVENTION AGAINST CORRUPTION, New York , 2004
74. UNITED NATIONS HANDBOOK ON PRACTICAL ANTI-CORRUPTION MEASURES FOR PROSECUTORS AND INVESTIGATORS (2004)
75. UNITED NATIONS *Office on Drugs and Crime* THE GLOBAL PROGRAMME AGAINST CORRUPTION UN ANTI-CORRUPTION TOOLKIT (2004)
76. Vincent Barry, **Philosophy a Text with Readings**(2nd,1983)
77. Worku Yaze Wodage; **Burdens of Proof, Presumptions and Standards of Proof in Criminal Cases** (2014)
78. Worku Yaze Wodage; **Criminalization of 'Possession of Unexplained Property' and the Fight against Public Corruption**(2014)
79. W. Todd Barron October 2017 St. John's, Newfoundland; **THE PEACE MODEL OF INVESTIGATIVE INTERVIEWING: A COMPARISON OF TRAINED AND UNTRAINED SUSPECT INTERVIEWERS**

## አባሪ1 የቅድመ እና የድህረ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስተ

ሰልጣኞች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች ስልጠና ከመጀመራቸው በፊት እና ስልጠና ከማጠናቀቃቸው በኋላ እንዲሞሉት ይጠበቃል፡፡

በቁጥሮች ትይዩ ባሉት ሳጥኖች ውስጥ የ √ ምልክትበማድረግ ምላሻችሁን አመላክቱ

| ተ.ቁ | ርዕሰ ጉዳይ | በርዕሰ ጉዳዩ ያለ የግንዛቤ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
| 1. | የስነምግባር ምንነት | | | | |
| 2. | የሙያ ስነምግባር ምንነት | | | | |
| 3. | ሙያዊ ሀላፊነትን መወጣት | | | | |
| 4. | በአድሎአዊነት አለመስራት | | | | |
| 5. | የሙያ ብቃትና ትጋት | | | | |
| 6. | ሀላፊነትና ተጠያቂነት | | | | |
| 7. | ቅንነት | | | | |
| 8. | ሀቀኝነት | | | | |
| 9. | ሙያዊ ስነምግባርን እንዴት ማዳበር ይቻላል | | | | |